ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 117 ታኅሣሥ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ







# ኢፕድ በአፋር ባዘጋጀው "ስለ ኢትዮጵያ" መድረክ፡-

## - የአገር ምሰሶ የሆኑትን ሰላም፣ አንድነትና ልዕልና ማጽናት እንደሚገባ ተገልጿል
## - አሻራ መጽሐፍ በአፋርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ተመርቋል

**አርዓያ ጌታቸው**

ሰመራ፡- ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአፋር ባዘጋጀው 13ኛው "ስለኢትዮጵያ" የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት ላይ ሶስቱ የአገር ምሰሶዎች የሆኑት ሰላም፣ አንድነትና ልዕልናን ማጽናት እንደሚገባ ተገለጸ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአፋርኛ ቋንቋ ያዘጋጀው አሻራ መጽሀፍም ተመርቋል።

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ፕሬዚዳንትና የኢፕድ ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ምህረት ደበበ በዚሁ ወቅት ባቀረቡት ጽሁፍ፤ ሠላም፣ አንድነትና ልዕልና የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው። ሠላምና አንድነትን ካሰፈንን ልዕልና የሁለቱ እሳቤ ውጤት ስለሆነ ይገኛል ብለዋል።

"ሰላም ሲባል ፍቅር ነው፤ መተሳሰብም ነው" ያሉት ዶክተር ምህረት፤ በዓለም የጤና ድርጅት ብያኔ መሠረትም ሠላም ከጤና ጋር ይያያዛል፤ ሁሉም ሰው ጤናማ ሆኖ የሚኖርባት አገር ስትኖርና ሠላም ሆና ስትቀጥል ብቻ አንድ አገር ሠላም ያላት ናት ተብሎ ይወሰዳል ሲሉ አስረድተዋል።

ብዙ ጊዜ ጦርነት ሲባል የማይወጣ ገንዘብ የማይመታ ከበሮ የለም ያሉት ዶክተር ምህረት፤ ለሠላም ሲሆን ግን ይህንን ያህል ገንዘብ ይበጀታል ወይ? ከበሮውስ ይደለቃል ወይ? ብሎ መጠየቅ ይገባል ሲሉም ነው የገለጹት፡፡

በሌላ በኩል ስለአንድነት ሲታሰብ አንዳንዶች አንድነትን መጨፍለቅ አድርገው የሚረዱ አሉ። ነገር ግን አንድነት ልዩነትን አስጠብቆ በአንድ የመቆም ምስጢር ነው ብለዋል።

አሁን ባለው አካሄዳችን የምንፈልገውን አንድነት ማምጣት እንችላለን ወይ የሚለውን በግብታዊነት ሳይሆን ቁጭ ብለን በመመካከር መመለስና መፍትሄ ማበጀት ይገባናል ሲሉም ተናግረዋል።

ልዕልና የሚለው እሳቤም የማንም ባሪያ ሣንሆን የራሳችንን ማንነት አሸንፈን ሃላፊነት በተሞላበት መንገድ

ኢፕድ በአፋር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ፎቶ - እዮብ ተፈሪ

አቶ ሚሊዮን ማቲዮስ

## በሩብ ዓመቱ 1.95 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ለማምረት ታቅዶ 1.38 ሚሊዮን ቶን ተመርቷል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- በ2015 የመጀመርያ ሩብ አመት በአገር አቀፍ ደረጃ በኢንዱስትሪዎች 1 ነጥብ 9 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ለማምረት ታቅዶ 1 ነጥብ 38 ሚሊዮን ቶን መመረቱን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ሚኒስቴሩ የሲሚንቶ ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት እየሰራ መሆኑን አስታውቋል፡፡

በሩብ ዓመቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ

## "ሠላምን፣ አንድነትንና ልዕልናን ለማምጣት ኢትዮጵያ አፋርን መሆን አለባት"

### - ሙዐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት

**አርዓያ ጌታቸው**

ሰመራ፡- ኢትዮጵያውያን ከአፋሮች ብዙ መማር ያለብን ጉዳዮች አሉ፤ ኢትዮጵያ ልክ እንደአፋር ልትሆን ይገባል ሲሉ ሙዐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ተናገሩ።

ሠላምን፣አንድነትንና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- ገበበ ገብሬ

## ጉባዔው አጋር ሲባሉ የቆዩ ድርጅቶችን ባለቤት በማድረግ ታሪካዊነቱን አስጠብቋል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዳማ፡- የብልፅግና ወጣቶች ሊግ በመጀመሪያ ጉባዔው አጋር ይባሉ የነበሩ ድርጅቶችን ባለቤትነት ባረጋገጠ መልኩ በማካሄድ ታሪካዊነቱን ማስጠበቁን ባወጣው የአቋም መግለጫ አስታውቋል።

"ለኢትዮጵያና አፍሪካዊ ብልጽግና የሚተጋ ወጣት" በሚል መሪ ሃሳብ ከታህሳስ 21-25/2015 ዓ.ም በአዳማ

ጉባዔው አጋር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ከወጪ ንግዱ ከ1 ነጥብ 5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

ገጽ 3

ዜና

# የገናና የጥምቀት በዓላትን ለማክበር ወደከተማዋ የሚመጡ ቱሪስቶችን ለመቀበል ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- የገናን እና የጥምቀት በአላትን ለማክበር ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ሌሎች የውጭ አገራት ቱሪስቶችን ለመቀበል ከፍተኛ ዝግጅት መደረጉን የአዲስ አበባ ከተማ ባህል ፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡ በከተማዋ ውስጥ ላሉ 170 ባለኮከብ ሆቴሎች የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ ብቃት የማረጋገጥ ስራዎች እየተሰራ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ባህል ፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደስታ ሎሬንሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ መጪውን የገና እና የጥምቀት በዓላትን ለመታደም የሚመጡ ቱሪስቶችን ለመቀበል እና ለማስተናገድ የተለያዩ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው፡፡

የገና እና የጥምቀት በዓላት በጦርነትና በኮቪድ ምክንያት የተቀዛቀዘውን ቱሪዝም በማነቃቃት ረገድ ፋይዳቸው ትልቅ ነው ያሉት አቶ ደስታ ፤ ለዚህም አዲስ አበባ ያላትን ሰፊ የቱሪዝም ሀብት በስፋት ለማስተዋወቅና ጎብኚዎች በሚያዩአቸው ስፍራዎች ተደስተው እንዲሄዱ ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

በዓሉን ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ፓኬጆችን በማዘጋጀት አስጎብኚ ድርጅቶች እንዲያስተዋውቁ እና የውጭ አገራት ቱሪስቶች በበዓላቱ እንዲታደሙ የሚደረግ መሆኑን አቶ ደስታ ገልጸው፤ ለሚመጡት ጎብኚዎች የሆቴል ፣ የትራንስፖርትና የሽያጭ ማዕከላት ከወዲሁ ዝግጁ እንዲሆኑ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

በተለይ ከተማው ውስጥ ያሉ እንደ አንድነት ፓርክ፣ ሳይንስ ሙዚየም፣ እንጦጦ ፓርክ እና ወዳጅነት ፓርክ ከሚጎበኙ ስፍራዎች ውስጥ ዋነኞቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

አቶ ደስታ እንደገለፁት፤ ቢሮው ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከከተማ አስተዳደሩ የጸጥታ አካላት፣ ከቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከፍትህ እና ከሌሎች የአስተዳደር አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት በዓላቱ ሰላማዊ እና ሀይማኖታዊ እሴታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ እየተሰራ ነው፡፡

በቱሪዝሙ ዘርፍ ጎብኚዎች የቆይታ ጊዜን ለማራዘም የሚያስችሉ ዝግጅቶች እየተሰሩ መሆናቸውን አመልክተው፤ ለሆቴል ማህበራት ፣ ለአስጎብኚ ድርጅቶች፣ ለቱር ኦፕሬተሮችና በቱሪዝም ዘርፍ ለተሰማሩ አጋር አካላት የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በመስጠት፣ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት እንዲስተካከሉ በማድረግና ቁጥጥር በማድረግ ቱሪስቶቹን በምቹ መስተንግዶ መቀበል የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው ብለዋል፡፡

በዓላቱን ለመታደም ለሚመጡ እንግዶች ጥሩ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ብሎም ከተማዋን ተወዳዳሪ የቱሪዝስቶች መዳረሻ ለማድረግ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አመልክተው፤ በዚህም በከተማዋ ውስጥ ላሉ 170 ባለኮከብ ሆቴሎች የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ የተለያዩ ሙያዊ ሥልጠናዎች በመስጠት ቁጥጥር የማድረግ እና ብቃት የማረጋገጥ ስራዎች እየተሰራ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

በቱሪዝምም ሆነ በሌሎች አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የተሰማሩ የግሉ ሴክተሮች ለቱሪስቶች የማይረሳ መልካም መስተንግዶ በመስጠት ራሳቸውንም ሆነ አገራቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ በትጋት መስራት እንደሚኖርባቸውም አሳስበዋል፡፡

እንደ አቶ ደስታ ገለጻ፤ የሰላም ስምምነቱ ለቱሪዝም ዘርፉ ትልቅ መነቃቃት ፈጥሯል፡፡ ይህም በተለይ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ያሉት ታሪካዊ የቱሪዝም መዳረሻዎች የቱሪስቶችን ፍሰት ይጨምራል፤ ከዚህም አዲስ አበባ ከተማ ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡

በመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከ240 ሺ በላይ ቱሪስቶች አዲስ አበባ ከተማን በመጎብኘታቸው ከ 13 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱም ታውቋል፡፡

## የገና ዛፍ ወጪን ለማስቀረት ለአገር በቀል ፈጠራዎች ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ተገለጸ

**መክሲት ወንድወሰን**



አዲስ አበባ፡- በውጭ ምንዛሬ ከውጭ የሚገባውን የገና ዛፍ ለመተካት የሚደረገውን አገር በቀል የፈጠራ ሥራዎች ማበረታታት ጠቃሚ መሆኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን የሰጡ አንዳንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ፡፡

እንደነዋሪዎቹ ገለጻ፣ የገና በዓል ለማክበር በውጭ ምንዛሬ ከውጭ የሚገባውን የገና ዛፍ መጠቀም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ባህል እየሆነ ነው፡፡ ነገር ግን በዘንድሮ ዓመት ይህንን የሚተካ ባህላዊ የበዓል ማድመቂያ ለገበያ እየቀረበ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ባህል የሚያንጸባረቅና በአከባቢው በሚገኘው ቁሳቁስ የገና ዛፍ ለመተካት የሚደረገው እንቅስቃሴ መደገፍ አለበት ያሉት ነዋሪዎቹ፤ ገና በዓል ሲከበር ሁሉም ዜጋ ለአገር በቀል የፈጠራ ሥራዎች ትኩረት በመስጠት ወጪን መቀነስ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት አቶ ፋሲካ ጸጋዬ እንደተናሩት፤ ቀደም ሲል የገና ዛፍን ገዝተው ይጠቀሙ ነበር፤ ነገር ግን ዘንድሮ ይህንን የሚተኩ በአገር ውስጥ በቀላል ቁሳቁስ የተሰሩ ማድመቂያዎችን በገበያ ላይ በማግኘታቸው ይህንን ለመጠቀም ወስነዋል፡፡

በዓላት ሲከበሩ ሁል ጊዜ የምዕራባውያኑን ባህል የሚገልጹ ፈጠራዎችን ከመጠቀም ኢትዮጵያዊ ይዘት ያሉ፤ ከአባቶች የተወረሱ ድንቅ ባህሎችን በጠበቀ መልኩ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

"ሰው ሰራሹ የገና ዛፎች አብዛኞቹ ፕላስቲክ በመሆናቸው አካባቢን የመበከል አቅማቸው ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ፋሲካ፤ የአገልግሎት ጊዜውን የጨረሰ ሰው ሰራሹ የገና ዛፍ ወደ ውጭ ሲጣል በቀላሉ ወደ አፈርነት ስለማይቀየር አካባቢን በእጅጉ ይበክላል ብለዋል፡፡

በከተማዋ የእንጨት እና ቅርጻ ቅርጽ ስራ በመስራት የሚተዳደሩት አቶ ፋሲል አድማሱ በበኩላቸው ባላቸው እውቀትም ሰው ሰራሹን የገና ዛፍ በአገር በቀል ቁሳቁስ ለመተካት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የገና በዓል ምክንያት በማድረግ በጣም ውብ የሆኑ የገና ዛፍ እና አጠቃላይ የበዓሉ ይዘት ያላቸውን የእንጨት ሥራዎችን የሕብረተሰቡ አቅም ባገናዘበ መልኩ ለገበያ እያቀረቡ ነው፡፡

ከእንጨትና በአካባቢው ከሚገኙ ግብዓቶች የሚሰሩ በዓሉን የሚያደምቁ ቁሳቀሶች በአንድ በኩል ከውጭ የሚገባውን ሰው ሰራሽ የገና ዛፍ የሚያስቀር ሲሆን በሌላው በኩል ደግሞ የገና ዛፍን ለመተካት የሚጨፈጨፉ ዛፎችን እንደሚታደግ አቶ ፋሲል ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ለሥራ እድል ፈጠራ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለውም አክለው ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው የከተማው ነዋሪ የሆኑት አቶ ዮሐንስ አርጋው በበኩላቸው፣ የፈጠራ ሥራዎቹ የአገሪቱን ባህልና ትውፊት ያገናዘቡ በመሆናቸው ሊበረታቱ ይገባል ብለዋል፡፡ እነዚህ አገር በቀል የፈጠራ ሥራዎች የአገልግሎት ጊዜያቸውን ከጨረሱ በቀላሉ ወደ አፈርነት የሚቀየሩ በመሆናቸው ብክለት እንደማያስከትሉም ተናግረዋል፡፡ ከገቢ አንጻርም ለሥራ አጥ ወጣቶች የገቢ ምንጭ እንደሚሆኑ ገልጸዋል፡፡

## ቀጣዩ የአየር ሁኔታ በሰብል ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በጥር ወር በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች እድገታቸውን ባልጨረሱ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የአየር ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ህብረተሰቡ እንደ አከባቢው ሁኔታ ሊከሰት ከሚችለው ተፅዕኖ ሰብሎቹን ለመከላከል የሚያስችሉ ስራዎችን እንዲሰራም አሳስቧል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የጥር ወር የአየር ሁኔታ አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ ፤ በጥር ወር በጋ ደረቅ ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ አየር ሁኔታ ጎልቶ በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ሊከሰት እንደሚችል የትንበያ መረጃዎቹ አመላክተዋል። የሌሊት እና የማለዳ ቅዝቃዜም በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች በቀጣይነት ሊከሰት እንደሚችል ገልጿል።

አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በኦሮሚያ ክልል በጥቂት ጅማ ፣ ኢሉባቦር እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በሰገን ሕዝቦች፣ ደቡብ ኦሞ እና ቤንች ማጂ ዞኖች ፤ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ በሲዳማ ክልል ፣ አማራ ክልል ሰሜናዊ እና ደቡብ ወሎ ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ዝናብ ይጠበቃል።

እንደ ኢንስትቲዩቱ ገለጻ ፤ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በመደበኛ ሁኔታ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ፣ ምስራቅ አማራ አካባቢዎች አነስተኛ መጠን ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የተቀሩት የአገሪቱ ክፍሎች ደረቅ የአየር ሁኔታ እንደሚኖራቸው ገልጸዋል።

ደረቃማው የአየር ሁኔታ ለድህረ ሰብል ስብሰባ በጎ ጎን አለው ያለው መግለጫው፤ በአንጻሩም ከደረቃማ አየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አከባቢዎች ቅዝቃዜው ቀጣይነት ስለሚኖረው እድገታቸውን ሙሉ በሙሉ ባልጨረሱ ሰብሎች በተለይ በመስኖ በሚለሙ ፍራፍሬ ተክሎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል። አርሶ አደሩ ቅዝቃዜውን ለማሻሻል የሚረዱ ስራዎችን በመስራት ለሰብሎቻቸው አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉም ጠይቋል።

በሰሜን ምስራቅ ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛው ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ደቡባዊ ክፍል እና ደቡብ ምዕራብ ሀገሪቱ ክፍሎች አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን እርጥበት ሊኖር እንምችል የጠቆመው መግለጫው፤ እርጥበቱ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በልግ እርሻ ቀድሞ ለሚጀምሩ አከባቢዎች የአፈር እርጥበት ስለሚጨምር አርሶ አደሩ ቶሎ የማሳ ዝግጅት እንዲያደርጉ አሳስቧል። በተለይ በደቡብ ሀገሪቱ ክፍሎች ለሚገኙ አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃ እና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ለማሻሻል የጎላ ሚና አለው ብለዋል።

ላይኛው ባሮ አኮቦ ፣ መካከለኛው እና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ ፣ ኦሞ ጊቤ ፣ መካከለኛው ገናሌ ዳዋ ፣ ዋቢሸበሌ እና መካከለኛ አባይ ተፋሰሶች አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከመጠነኛ እርጥበት ጀምሮ እርጥበታማ መሆን እንደሚችሉ ትንበያው መረጃ ውጤት አመላክቷል። ከዚህ የተቀሩት አብዛኛው ተፋሰስ አካባቢዎች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ አየር ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል ገልጿል።



ቁምነገር እውነቱ

# ከወጪ ንግዱ ከ1 ነጥብ 5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት ከወጪ ንግድ 1 ቢሊዮን 528 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ መገኘቱን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የሚኒስቴር መስሪያቤቱ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ ቁምነገር እውነቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገጹት፣ በ2015 በጀት አመት በአምስት ወራት ውስጥ የተለያዩ የወጪ ንግድ ምርቶችን ለወጪ ገበያ በማቅረብ 1 ቢሊዮን 528 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡

በበጀት አመቱ የተለያዩ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ 1 ቢሊዮን 899 የአሜሪካ ዶላር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 1 ቢሊዮን 528 የአሜሪካ ዶላር ገቢ መሰብሰቡን የገለጹት ስራ አስፈፃሚዋ፣ ለወጪ ገበያ ቀርበው ገቢ ከተገኘባቸው የወጪ ንግድ ዘርፎች ውስጥ የግብርና ምርቶች 78 ነጥብ 4 በመቶ፣ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ11 ነጥብ 9 ፣ ጨርቃጨርቅና አልባሳት 90 ነጥብ 96 በመቶ፣ ማዕድን ዘርፍ 6 ነጥብ 3 በመቶ እንዲሁም ከሌሎች ዘርፎች 3 ነጥብ 43 በመቶ ድርሻ እንደነበራቸው ጠቁመዋል፡፡

ከቁም እንስሳት ፍየልና በግ ለዓለም አቀፍ ገበያ አቅርቦት 83 በመቶ ድርሻ በመያዝ በጋማ እንስሳት የወጪ ንግድ ላይ ግሽበት እንዳለም ጠቁመዋል፡፡

ከፍተኛ ላኪ ድርጅቶች በተቀላጠፈ አገልግሎት ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ወቅቱን ጠብቀው ባለማቅረባቸው በወጪ ኢኮኖሚው ላይ ግሽበት አስከትሏልም ብለዋል፡፡

የዘንድሮው የወጪ ንግድ የአምስት ወራት አፈፃጸም ከ2014 ዓ.ም ተመሳሳይ ወቅት አፈፃጸም ጋር ሲነፃፀር የ90 ነጥብ 092 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ቅናሽ ማሳየቱንም ስራ አስፈጻሚዋ ጠቁመዋል፡፡

በሕገ ወጥ ንግድና በኮንትሮባንድ የቀይ ቦለቄና የዥጉርጉር ቦለቄ ምርት በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ለገበያ እየቀረበ መባከንና የማሾ ምርት በዓለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊነቱ መቀዛቀዝ በጥራጥሬ የወጪ ንግድ አፈፃፀሙ ላይ ግሽበት ማምጣቱን ተናግረዋል፡፡

የጥቁር ገበያ መስፋፋት በወጪ ምርቶች የዋጋ ግሽበት በማስከተሉ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማድረሱን ገልጸዋል፡፡

በኢቨስትመንት እርሻ የተመረቱ ምርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው ለዓለም አቀፍ ገበያ መቅረብ ባለመቻላቸው በገቢ ግኘቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረሱን በመግለጽ በተለይም የሰሊጥ ምርት በሚመረትባቸው አካባቢዎች በቤሻኒሻንጉል ጉሙዝና በወለጋ በሰላምና በጸጥታ ችግር ምክንያት ምርቱን በወቅቱ ለገበያ በማቅረብ ሂደት ላይ እንቅፋት መግጠሙን አብራርተዋል፡፡

ለላኪ ድርጅቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በዓለም አቀፍ ገበያ ዋጋ ምርታቸውን እንዲልኩ የማድረግ ስራ መጀመሩን ገልጸው ከፍተኛ ገበያ ያላቸው ላኪዎች ምርታቸውን ቅድሚያ ግብይት ፈጽመው የሚልኩበት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን አብራርተዋል፡፡

የቅባትና ጥራጥሬ ምርቶችን ጥራት አሻሽለው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ላኪዎችን በመለየት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ምርታቸውን ወደ ውጭ መላክ እንዲችሉ የጋራ መግባባት ለመፍጠር እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የሕገ ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት አሳሳቢነት ድረጃ መድረሱን ጠቅሰው ችግሩን ለመቅረፍ ደረጃ በደረጃ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

# ማዕከሉ ለ70 ሺህ የካንሰር ህሙማን አገልግሎት መስጠት ያስችላል

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**



ዘመናዊ የካንሰር መመርመሪያ ማሽን

አዲስ አበባ፡- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የካንሰር ማዕከል የማስፋፊያ ግንባታው ሲጠናቀቅ ከ70 ሺህ በላይ ለሚሆኑ የካንሰር ህሙማን አገልግሎት መስጠት እንደሚያስችል የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ገለጸ።

በሆስፒታሉ የካንሰር ስፔሻሊስት የሆኑት ዶክተር አብዱ አደም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሁን ባለ መረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት ከ70 ሺህ በላይ የካንሰር ህሙማን በተለያዩ የካንሰር ማዕከላት ህክምና ያገኛሉ። ይህ የካንሰር ማዕከል ሲጠናቀቅ ግን በተለያየ ቦታ ይታከም የነበረውን ሰው በአንድ ቦታ በመሰብሰብ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ያደርጋል ተብሎ ታምኖበታል።

አሁን በመሰራት ላይ ያለው የካንሰር ማዕከል በሀገሪቱ ትልቁ የካንሰር ማዕከል ሲሆን፤ አምስት የጨረር ማሽኖችንና ከሶስት መቶ በላይ የታካሚ አልጋዎች ይኖሩታል፤ በተወሰኑ የአፍሪካ ሀገራት ብቻ የሚገኘው ‘ሳይክሎትራም’ መሳሪያዎችንም ይይዛል የሚሉት ዶክተር አብዱ፤ ካንሰር በኢትዮጵያ በዓመት ከሚሞቱ ሰዎች ውስጥ ሰባት በመቶውን ይሸፍናል። ስለሆነም በበሽታው የሚሞተውን ሰው ቁጥር ለመቀነስ የማዕከሉ ግንባታ እጅግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር አብዱ ገለጻ፤ ማዕከሉ ለካንሰር ታካሚዎች እፎይታን የሚፈጥር ነው፤ የሚገፈልጉትን ህክምና በሚፈልጉት ደረጃ ማግኘት ያስችላቸዋል። ከሙያ አንፃርም የህክምና ባለሙያዎች ያላቸውን እውቀት ተጠቅመው በተሟላ ሁኔታ ታካሚዎቻቸውን እንዲከታተሉና ሙያዊ እርካታን እንዲጎናፀፉ ያደርጋቸዋል። በተመሳሳይ ህሙማን ወደ ውጭ ሀገር እንዳይሄዱና ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ እንዳያወጡ የሚያደርግ በመሆኑ እንደአገርም የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቀነስ ፋይዳው የጎላ ነው።

ዶክተር አብዱ እንደገለጹት፤ የኒውክለር ሜድስን ሰርቪስ አሁን ላይ በሀገራችን የሚሰጥ ምርመራ አይደለም። ማስፋፊያው ሲጠናቀቅ ግን አገልግሎቱ በአገር ውስጥ መሰጠት ስለሚጀምር ለህሙማኑም ሆነ ለሀገር የሚኖረው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ ነው። ማዕከሉ ከካንሰር ህክምናው በተጨማሪ የመቅኔ ንቅለ ተከላ አገልግሎትም ይሰጥበታል።

ማዕከሉ ሜዲካል ቱሪዝም ላይ ትልቅ ጠቀሜታን የሚሰጥ እንደሆነ የሚጠቁሙት ስፔሻሊስቱ፤ እስከዛሬ ድረስ ለህክምና ወደ ሌሎች ሀገራት የሚሄዱት ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው። በማዕከሉ ግንባታ ግን ከሌሎች ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል። ከሌሎች ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ህሙማን ተበራከቱ ማለት ደግሞ ሀገሪቱ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሬ ከፍ ያደርገዋል። ስለሆነም የማዕከሉ መጠናቀቅ ለሀገር ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያስገኛል ብለዋል።

እንደ ዶክተር አብዱ ማብራሪያ፤ ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ በ2016 የተጀመረ ቢሆንም በ2020 እና በ2021 መጨረሻ ይጠናቀቃል ተብሎ ታስቦ እስካሁን አልተጠናቀቀም። ለዚህ ደግሞ ወቅታዊ የገበያ ሁኔታው በተለይ የግንባታ ግብአቶች ዋጋ መናር ለግንባታው ተግዳሮት ሆኗል። ይህ በመሆኑም የጨረር ህክምና መስጫ ማሽኖች የሚቀመጡበት ክፍል የተወሰነ ክፍል ግንባታ ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ ባለበት ከቆመ ወራት አልፈዋል።

‹‹የህክምና እቃዎች ብቻቸውን ጥቅም የላቸውም፤ ማሽኖቹን የምናስቀምጥበት ቤት የግንባታ እቃ እጥረት ስላለብን ሊያልቅ አልቻለም።›› የሚሉት ዶክተር አብዱ፤ የሚመለከታቸው አካላት መጥተው ሥራው ያለበትን ደረጃ ጎበኝተዋል፤ ያጋጠሙንን ችግሮች በባለሙያዎች ገለፃ ተደርጎላቸዋል። ነገር ግን ወደ ተግባር የተለወጠና የተሰጠን መፍትሄ የለም ብለዋል።

ሌሎች ፕሮጀክቶች ሲዘገዩ የምናጣው ገንዘብ ሊሆን ይችላል፤ በጤና ዘርፉ ላይ ግን ፕሮጀክቶች ሲዘገዩ የምናጣው የሰው ሕይወት ነውና እንደመንግሥት የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም አሳስበዋል።

ሆስፒታሉ በሁለት ቢሊዮን 768 ሚሊዮን 21 ሺህ ብር ጠቅላላ በጀት ከሦስት ኮንትራክተሮች ጋር በመፈራረም የካንሰር ህክምና ማዕከል እና የልብ ህክምና ማዕከልን እያስገነባ መሆኑ ታውቋል።

# በሚዛን አማን ከተማ ሕገወጥ የመሬት ወረራ ባካሄዱ አካላት ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ሚዛን አማን፡- በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተከሰተውን ጦርነት ከለላ በማድረግ የመሬት ወረራ ባደረጉ አካላት ላይ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የሚዛን አማን ከተማ ከንቲባ አቶ ግሩም ተማም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የነበረውን ጦርነት እንደጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም በሚዛን አማን ከተማ ከፍተኛ የሆነ የመሬት ወረራ ተደርጓል።

በወቅቱ ሀገር የነበረችበትን ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ የመሬት ወረራ ሲያካሂዱ የነበሩ አካላት ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሳይወሰድ ቆይቷል። ሆኖም በተደረጉ ተጨማሪ ማጣራቶች በሀገሪቱ የነበረውን ጦርነት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ሕገ ወጥ ቤት ግንባታ ማካሄድ፣ የወል መሬት ወረራ፣ የተጋነነ ካሳ እንዲከፈል ማድረግ፣ የሰነድ መሰረዝና ማጥፋት፣ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ፍትህ የማዛባት ወንጀል ተሠርቷል።

አስተዳደሩ ይህን መነሻ በማድረግም እርምጃዎችን መውሰድ ጀምሮ በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ ከስድስት ሄክታር መሬት በላይ ነፃ ማውጣት ተችሏል። በዚህም የተሳተፉ ወደ ሃምሳ የሚጠጉ የአካባቢው ነዋሪዎችና አመራሮች ላይ እርምጃ ተወስዷል ብለዋል።



አቶ ግሩም ተማም

በዚህ ሂደት በመንግሥት ግብረ ኃይል ላይ ጥቃት ለመፈጸም የሞከሩ 15 ግለሰቦች ላይ ክስ ተመስርቶ በሂደት ላይ ነው መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ ዋና ማጠንጠኛ የሆነውን መሬት በአግባቡ በመምራትና በማስተዳደር በኩል በየደረጃው የሚገኝ ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት በኩል በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ ያሉት አቶ ግሩም፤ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ለአመራሩና ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ተሰጥቷል ብለዋል።

ከአመራሩ ባሻገር የመሬት ወረራ ሲፈጸም ቴክኒካል ነገሮችን ሲያመቻቹ የነበሩ ባለሙያዎች ከስራ ገበታቸው መታገዳቸውን አንስተውም፤ በጉዳዩ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ አካላት ማህደራቸው ተጣርቶ ጉዳያቸው ወደ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ መመራቱን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ግሩም ገለፃ፤ የመሬት ወረራን ለመከላከል የማጣራትና ኦዲት የማድረግ ስራው ሲሰራ ወደ መንግሥት ካዝና የሚገባው መሬት እንደተጠበቀ ሆኖ መሬቱ የአርሶ አደር ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ለአርሶ አደሩ የመመለስ ስራ ይሰራል።

የሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲሁም ሰፊ የመልካም አስተዳደር ችግር የሚነሳበት የመሬት ወረራን ለመቀልበስ አመራሩ መርህንና የመንግሥትን አሰራር ተከትሎ መስራት አለበት። ይህንን በማያስፈፅም መሪ ላይ ተጠያቂ የሚሆንበት ሥርዓት መዘርጋቱንም ገልጸዋል።

በከተማው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ብዛት ተከትሎ በስፋት የሚስተዋለውን የሕገ-ወጥ የመሬት ወረራ ለመቀልበስ ከተማ አስተዳደሩ ከዚህ በፊት ሲጠቀምበት የነበረውን አሰራር ለሕገ-ወጥነት የሚጋለጥ ሆኖ በማግኘቱ የመሬት አስተዳደር የአሰራር ማሻሻያዎች እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

# ኅብረተሰቡ የገና በዓልን ሲያከብር ድንገተኛ አደጋ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ኅብረተሰቡ የገና በዓልን ሲያከብር ድንገተኛ አደጋ እንዳይከሰት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

በዓሉን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት በሰጠው መግለጫ ኅብረተሰቡ የገና በዓልን ሲያከብር ድንገተኛ አደጋ እንዳይከሰት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ አሳስቧል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ታረቀኝ ወርቅነህ በመግለጫው እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት በገና በዓል ለሚፈጠሩ አደጋዎች ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ ቡድን አቋቁሟል። ነገር ግን ኅብረተሰቡ በዓሉን ሲያከብር ድንገተኛ አደጋ እንዳይከት ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል።

ጽህፈት ቤቱ የገና በዓል በሰላም እና በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረጉን ተናግረው፤ የውሃና የመብራት አገልግሎት ችግር እንዳይከሰት ከፍተኛ ሥራ ተሰርቷል ብለዋል።

“በበዓሉ ከፍተኛ የሆነ የኃይል ጫና ይኖራል። በዚህም አልፎ አልፎ የሚፈጠር የመብራት መቆራረጥ እንዳይከሰት ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል” ያሉት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ፤ የሚፈጠሩ ችግሮችን በአስቸኳይ የሚፈታ የጥገና ባለሙያ ቡድን ተቋቁሟል ብለዋል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋዜማው ከፍተኛ ኃይል የሚጠቀሙ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች በተቻላቸው መጠን በቀኑ ከፍተኛ ኃይል ባይጠቀሙ ተመራጭ ነው ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ ነዋሪዎችም ኤሌክትሪክ የሚጠቀሙበትን ሰዓት ቢመርጡ የተሻለ እንደሚሆን አሳስበዋል።

ከዚህ ባለፈ ነዋሪው የኤሌክትሪክ ኃይል የሚጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች በተደጋጋሚ ፍተሻ እንዲያደርግም አሳስበዋል።

በበዓሉ አከባበር ወቅት ድንገተኛ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ችግሮችን በ903 ነፃ የስልክ መስመር፣ ለእሳትና ድንገተኛ አደጋ በ939፣ ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ችግር በ905፣ ከጽዳት ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥሙ ችግሮች በ6199 ነጻ የስልክ መስመር መደወል እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

በመጨረሻም ምክትል ሥራ አስኪያጁ ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች መልካም የገና በዓል ተመኝተዋል።

# ኢፕድ በአፋር ባዘጋጀው...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የምንኖርበት የነጻነት መንገድ መሆኑን በመጥቀስ እይታቸውን አቅርበዋል።

አገር አስተሳሰብና የአስተሳሰብ ውጤት ነው ያሉት ዶክተር ምህረት፤ አገር የሚፈርሰው ሃሳብ ሲፈርስ፤ ሠላም የሚመጣው ሃሣብ ሠላም ሲሆን ነው ብለዋል።

በመድረኩ ሌላኛው ጽሁፍ አቅራቢ የአፋር ክልል የብልፅግና ፅህፈት ቤት የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ አቶ መሐመድ አሕመድ በበኩላቸው አገር የሠላም፣ የአንድነት እና ልዕልና ድምር ውጤት ናት፤ እነዚህ ሦስት ጉዳዮች የአገር ምሰሶዎች መሆናቸውን ተረድቶ ማጽናት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ መሀመድ አክለውም፤ ሠላም ዋጋው ብዙ ቢሆንም ሠላም ሲኖር ብዙ ጊዜ ትኩረት አንሰጠውም፤ ዋጋውን የምናውቀው ሠላምን ስናጣ ነውና ይህን ዕውነታ መረዳትና ሠላምን ማጽናት ይገባል ብለዋል።

ያለሰላም አገራዊ አንድነት አይረጋገጥም ያሉት አቶ መሀመድ፤ በመሆኑም ሰላምን ዘላቂ ማድረግ አንድነትንም ማጽናት መሆኑን አውቆ መስራት እንደሚገባ አስረድተዋል።

የአንዱ ታሪክ ከሌላው ጋር የተሳሰረ ነው፤ ይህ ዕውነት የማይለወጥ በመሆኑ ችግር ካለም በይቅርታና በአንድነት መንፈስ በመፍታት አገራዊ አንድነትና ሠላምን ማስቀጠል ይገባል ነው ያሉት አቶ መሐመድ።

በዚህ አግባብ ዘላቂ የሆኑትን ሰላምና አንድነትን በመጠቀም አገራዊ ልዕልና መፍጠር ይቻላል። ከዚህ ባለፈ በጎ ነገሮችን ማጉላት፤ አንድነትን የሚሰብኩ አንደበቶችንም ማብዛት ከተቻለ አገራዊ ልዕልና ይረጋገጣል ሲሉ አቶ መሀመድ ተናግረዋል።

የመወያያ ጽሁፍ ያቀረቡት አቶ የሺዋስ አሰፋ በበኩላቸው፤ ሕግ ማስከበርና ውይይት አብረው መሄድ ያለባቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ሕገ መንግሥቱን ጨምሮ ሕጎቻችን ችግር ያለባቸው ናቸው ብለን ብናምንም እንኳ ከሕግ አልባነት ይሻላሉና ማንም ከሕግ በላይ እንዳይሆን ሥርዓት ለማስያዝ ሕግ ማስከበር ይገባል ሲሉ አቶ የሺዋስ ተናግረዋል።

ማህበረሰቡ አሁን ያለበትን ችግር ሊሻገር የሚችለው ሕግ ሲከበርና ረባሾች ሲቀጡም ጭምር ነውና ይህንን ማወቅና መተግበር እንደሚገባ አስረድተዋል።

አቶ የሺዋስ እንዳስታወቁት፤ ከሕግ ማስከበር ባለፈ ሰላም ማስጠበቂያ አንዱ መንገድ ውይይት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ የጀመረውን ሥራ አጠናክሮ መቀጠልና መፍትሄ ማምጣት አለበት።

በእለቱም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአፋርኛ ቋንቋ ያዘጋጀው አሻራ መጽሐፍ ተመርቋል።

መጽሐፉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ካደረጉት የመጀመሪያ ንግግራቸው ጀምሮ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያደረጓቸው ንግግሮችን ይዟል።

በመጽሐፍ ምረቃው ላይ የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ሀጂ አወል አርባ፤ ፤ ኢፕድ መጽሐፉን በአማርኛ ቋንቋ አሳትሞ ሲያስመርቅ በሌሎች ቋንቋዎች ለማሳተም የገባውን ቃል አክብሮ በአፋርኛ ቋንቋ በማሳተሙ ምሥጋና ይገባዋል ብለዋል።

የኢፕድ ሥራ አመራር ቦርድ አባል ከይረዲን ተዘራ (ዶክተር) በበኩላቸው፤ በፌዴራል ደረጃ ያለ ተቋም በክልል ቋንቋ መጽሀፍ ማዘጋጀት ትልቅ ተግባርና ለሌሎችም ምሣሌ የሚሆን ነው ብለዋል።

በሰመራ የተከፈተውን ስለኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሀጂ አወል አርባ፣ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ዮናስ አዳዬ፣ ወይዘሮ ነቢሀ መሀመድ እና የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ፕሬዚዳንት ዶክተር ምህረት ደበበ ከፍተውታል።

በአውደርዕዩ ከ1950ዎቹ ጊዜያት አንስቶ የነበሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወሳኝ ሁነቶች ፣ በታሪክ አንጓዎች የተከሰቱ የሕዝብ ጥያቄዎች እንዲሁም ለአገር ሉዓላዊነት የተከፈሉ መስዋዕትነቶችና ከኢትዮጵያ የልማት ጉዞዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ለዕይታ ቀርበዋል።

# በሩብ ዓመቱ 1.95 ሚሊዮን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዮስ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በአሁኑ ወቅት ለሲሚንቶ እጥረት ዋነኛው መንስኤ የምርት እጥረት ነው። ለዚህ ደግሞ ፋብሪካዎች በአቅማቸው ልክ ማምረት አለመቻላቸው ነው።

ለሲሚንቶ የሚውሉ ግብዓቶች ስምጥ ሸለቆ፣ ዓባይ ሸለቆ ሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ በመሆናቸውና በአገሪቱ አልፎ አልፎ በሚስተዋሉ የፀጥታ መደፍረሶች ግብዓቶችን ከመገኛ ስፍራቸው እስከ ፋብሪካ ለማድረስ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደነበሩም ሚኒስትር ዴኤታው ጠቁመዋል።

ፋብሪካዎች ጥሬ ግብዓቶችን እንዳያወጡ ማድረግ፣ ማሽነሪዎችን ማቃጠል እና የመሳሰሉት የምርት ሂደቱን የሚያስተጓጉል በመሆኑ በሲሚንቶ ምርት አቅርቦት ላይ መስተጓጎል ተፈጥሯል። በተጨማሪም በሲሚንቶ ምርት ግብይት ላይ ማጭበርበሮች እና የተለያዩ ፍላጎቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

እነዚህን ለመፍታትም ተደጋጋሚ መድረኮች ተዘጋጅተዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ጉዳዩን ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ጭምር ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግለት ነው ብለዋል። ከአጭር ጊዜ አኳያ የሚፈጠሩ የፀጥታ ችግሮችን ከክልል መንግሥታትና ኢንዱስትሪዎች ጋር በመሆን ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያን 20 ከመቶ የሲሚንቶ ፍጆታ የሚሸፍነው እና በትግራይ ክልል የሚገኘው መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ወደ ሥራ ሊገባ ነው። በትግራይ ክልል በማዕድን ዘርፍ ፈቃድ የነበራቸው ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ወደ ሥራ እንዲገቡም እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ምርት አቁሞ የነበረው መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ በአሁኑ ወቅት ወደ ምርት እንዲገባ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት መደረጉን የጠቆሙት አቶ ሚሊዮን፤ ፋብሪካው 20 ከመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን የሲሚንቶ ፍጆታ የሚሸፍን ነው ብለዋል።

በመሆኑም ይህ ፋብሪካ ወደ ሥራ ሲገባ እና ሌሎች ኢንዱስትሪዎች የሚፈታተናቸው የግብዓት አቅርቦት ከተስተካከለ አቅርቦቱ እየጨመረ የሚሄድ ይሆናል። መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ወደ ሥራ ሲገባ በአገሪቱ የሚስተዋለውን የሲሚንቶ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ ያቃልላል ብለዋል።

በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል የተፈጠረውን ሠላም መነሻ በማድረግም ሚኒስቴሩ በበጀት ዓመቱ ያቀዳቸው እቅዶችን የማስተካከልና የመከለስ ሥራዎችን የሚያከናውን ይሆናል ያሉት አቶ ሚሊዮን፤ ከዚህ በተጨማሪም በትግራይ ትልቅ የማዕድን ሀብት በመኖሩ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል።

ቀደም ሲል በማዕድን ዘርፍ ፈቃድ አውጥተው የገቡ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችም ተመልሰው በትግራይ ክልል ሥራ የሚጀምሩበት ሁኔታዎች እየተመቻቹ ነው። አካባቢው በጦርነት ላይ የነበረ ስለሆነ በክልሉ ፈቃድ አውጥተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ባለሀብቶችና ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ደብዳቤ መፃፉንና ጥሪ መደረጉንም አስገንዝበዋል። በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረትም እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ጉዳት የደረሰባቸውንም የማገዝና ወደ ሥራ የማስገባት ሥራ ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው ሚኒስትር ዴኤታው አረጋግጠዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ከሆነ፤ የሲሚንቶን እጥረት ለማቃለል ትኩረት ተሰጥቶ እየሰራ ነው። ያም ሆኖ ግን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት መፍትሄው ምርት መጨመር መሆኑን አስገንዝበዋል።

# ጉባዔው አጋር ሲባሉ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ከተማ ሲካሄድ የቆየው ጉባኤ በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል፡፡

ጉባዔው ከዚህ ቀደም የነበረው የአባልና አጋር ግንኙነት ተወግዶ ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የሊጉ አባል የሆኑ ወጣቶች በፍትሐዊ ውክልና የተሳተፉበት የመጀመሪያውና ታሪካዊ በማድረግ መጠናቀቁን የወጣው የአቋም መገለጫ ያትታል።

ከለውጡ በፊት ኢህአዴግ በመራባቸው ዓመታት የተሠሩ መልካም ሥራዎችና የተመዘገቡ ውጤቶች እንደነበሩ ያወሳው መግለጫው፤ ሆኖም የኢፍትሐዊነት፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የዴሞክራሲ እጦት፣ የብልሹ አሠራሮችንና የተደራጁ የሌብነት ችግሮችን አምርረው በመቃወም በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣና ብልፅግና ፓርቲ እውን እንዲሆን በተደረገው ወሳኝ የትግል እንቅስቃሴ ውስጥ የወጣቶች ሚና እጅግ ከፍተኛ ነበር ብሏል፡፡

በትግሉም ወጣቶች በሃሳብ ከመታገል እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል ሲል አክሏል፡፡

ቀጥሎም ለውጡ ጥቅማቸውን ባሳጣቸውና ወደ ኋላ እንዲመለስ ያላቸውን ኃይል ሁሉ በሚጠቀሙ እና ለውጡ ወደ ፊት እንዲራመድና ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን ብልፅግና ለማምጣት በሚታገሉ ኃይሎች መካከል በነበረው እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ ለውጡ ወደ ፊት እንዲራመድ በማድረግ ረገድ የወጣቶች በተለይም የብልፅግና ወጣቶች ሊግ መዋቅር ሚና ከፍተኛ እንደነበር አስረድቷል፡፡

ባለፉት በጣት በሚቆጠሩ የለውጥ ዓመታት በኢትዮጵያ እውነተኛ ህብረብሔራዊ ፌዴራላዊ ሥርዓትን ለመገንበት ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ወንድማማችነትና እህትማማችነት እንዲጎለብት፣ ኢኮኖሚ እንዲያድግና የዜጎች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ለተሠሩ ሥራዎችና ለመጡ ውጤቶች ጉባዔው እውቅና የሚሰጥ መሆኑም ተመላክቷል።

በአፍሪካ ብሎም በኢትዮጵያ ውስጥ ወጣቶች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙ የህብረተሰብ ክፍል ሲሆኑ እስካሁን ድረስ ይህንን የሚመጥን ፖለቲካዊ ተሳትፎም ይሁን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነቱ ሲረጋገጥ አይታይም ያለው መግለጫው፤ ይህ ነባራዊ ሁኔታ ግን አንድ ወቅት ላይ በቃ ሊባል ግድ ነው፡፡ ለዚህም ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው ሲል አክሏል።

ለዚህም ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በየደረጃው በማጠናከር የሚያጋጥሙ እንቅፋቶች በተባበረ ክንድ በመመከት መሻገርና የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ወጣቱ ሊተጋ ይገባል ብሏል፡፡

በፖለቲካዊ ጉዳዮች መሳተፍም ይሁን በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ተጠቃሚ መሆን በወጣቱ ጥረት የሚረጋገጥ እንጂ ማንም ከየትም ሊቸረው የሚችለው የበጎ ፍቃድ ስጦታ አይደለም፤ በመሆኑም በየደረጃው ለተሻለው ውጤት ያላሰለሰ ጥረት እና ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል ብሏል።

የወጣቶች ሊግ ተጠናክሮ በመውጣት የወጣቱን ኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሆኖ እንዲወጣ መሥራት ይኖርበታል ያለው የአቋም መግለጫው፤ ለዘላቂ ሰላምም የወጣቱ ሚና የጎላ እንዲሆን በትኩረት እንደሚሠራ አስታውቋል።

የዓባይ ግድብ፣ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲን በመሳሰሉ የተለያዩ የአገር ጉዳዮች ላይ በብርታት እንደሚሠራም መግለጫው አትቷል።

# “ሠላምን፣ አንድነትንና...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአፋር ክልል በሠመራ ከተማ ባዘጋጀው 13ኛው "ስለ ኢትዮጵያ" የፓናል ውይይት ላይ ጽሁፍ ያቀረቡት ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት መላ ኢትዮጵያውያን ከአፋር ብዙ ልንማራቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ ሲሉ ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

ብዙ ጊዜ ወደ ምዕራቡ ወደ ምሥራቁ ሄደን እውቀት ለመቅሰም የምናደርገውን ጥረት ያህል ወደ ማህበረሠባችን ገብተን ባህሉንና ያለውን ጥበብና እውቀት የመቅሰም ልምድ የለንም፤ አለን ከተባለም ለጥናት ብቻ ነው ብለዋል፡፡

አፋሮች ታሪካቸውን በደንብ ያውቃሉ፤ ለልጆቻቸውም በደንብ ይነግራሉ፤ ይህ ትልቅ እሴት በመሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያንም እንደ አገር የኖርንበትን ድክመትና ጥንካሬ በደንብ ማወቅና እንደ አፋሮች ለልጆቻቸው ተገቢ በሆነ መልኩ ማስተላለፍ አለብን ብለዋል።

እያንዳንዱ ማህበረሰብ ለልጆቹ ታሪክ የሚነገርበት ባህል ሊኖረው ይገባል ያሉት ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል፤ አፋሮች ማንነታቸውን ከኢትዮጵያዊነት ጋር አጣጥመው መኖራቸውን ገልጸዋል።

"እንኳን እኛ ግመሎቻችን የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ያውቃሉ" የሚለው የአፋሮች ንግግር አፋርነት ከኢትዮጵያዊነት ጋር ተጣጥሞ የቀጠለበት ጥበብ ነው ሲሉም ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል አስረድተዋል።

በአፋር ክልል አፋርነትና ኢትዮጵያዊነት ተጣልቶ አያውቅም፤ ይሄንን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊቀስመው የሚገባው ሀብት ነው ብለዋል።

ሙዐዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል እንዳስታወቁት፤ በአፋር መረጃን ማንጠር መቻላቸው ትልቁ ባህል ነው። ሌላው ማህበረሰብም ይህንን ባህል ማድረግ አለበት፤ አፋሮች መረጃን እንዳለ አይለቁም፤ አንጥረው ነው፤ ሌሎች ማህበረሰቦችም መረጃን የመለየትና የማንጠር ባህል ሊኖራቸው ይገባል።

ከአፋር ልንማር የሚገባን ሌላኛው ጉዳይ የመነጋገር ባህላቸውን ነው ያሉት ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል፤ ሁሉም በየደረጃው በየባህሉ የመነጋገርና የመወሰን ባህልን ማዳበር ያስፈልጋል ብለዋል። በጋራ በመወሰን መመራት ከተቻለም አንድነትን ማምጣት ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል።

በአፋር ሽማግሌ፣ የጎሳ መሪ እና የሃይማኖት አባት ይደመጣል፤ መረጃ ሲመጣ ማነው ያለው ተብሎ ተጠይቆ ከእነዚህ አዋቂዎች ከመጣ ብቻ ተቀብሎ ይተላለፋል፤ ይተገበራል፤ ይህ እሴት በሀሰተኛ መረጃ ለምትታመሰው ኢትዮጵያ ትልቅ ትምህርት ነውና መቅሰም ይገባናል ብለዋል።

እንደ ሰንደቅ ዓላማ ላሉ ትዕምርቶቻችን ክብር እንስጥ ያሉት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፤ ለየአካቢዎቻችን መሪዎች፣ አዋቂዎች፣ ሕግና ሕጋዊ ተቋማት እንዲሁም መሰል ምልክቶቻችን ሁሉ ክብር መስጠት ይገባናል፤ ይህንንም ከአፋሮች የምንማረው እውነታ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ሕገመንግሥታዊነት ትዕምርት ነው፣ መከበር አለበት፤ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ችግር ካለ ያንን እንደ አፋሮች ባህል በመነጋገር መረጃን አንጥሮ በመለየት ማሻሻል ይቻላል ብለዋል።

ሌላው ከአፋር መማር ያለብን ጀግንነትን የመናገርና የመዘከር ባህል ነው ያሉት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፤ በአፋር ጀግንነት ይነገራል፣ ይዘከራል፤ ስለዚህ የደረሰብን ክፉ ክፋውን ሣይሆን መልካሙን በመንገር ለልጆቻችን ማሻገር ይገባናል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደአገር አሸንፈን ሠላምን፣ አንድነትንና ልዕልናን ማምጣት እንድንችል ኢትዮጵያ አፋርን መሆን አለባት" ሲሉ ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መተማመንን ለሚፈጥሩና ለሚያጠናክሩ ተግባራት ቅድሚያ እንስጥ!

ግጭቶች በባህሪያቸው ሊያስከፍሉ የሚችለው ዋጋ በቀላሉ ሊገመት የማይችል፤ ከተከሰቱም በኋላ ለማስቆም ያለው ፈተና ከፍ ያለ ነው፤ ከዚህ የተነሳም ከግጭት በኋላ የሚገኘን ሰላም ዘላቂ ማድረግ ከፍተኛ ቁርጠኝነት፤ ብዙ ዋጋ መክፈልንም የሚጠይቅ ነው።

የታሪክ ድርሳናት እንደሚያመለክቱት ሀገራት አንድ ጊዜ እርስ በርስ ግጭት ካጋጠማቸው በኋላ ተጨማሪ የእርስ በርስ ግጭቶችን የማስተናገድ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። እ.አ.አ በ2010 በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ስለ እርስ በርስ ግጭቶች ማገርሸት እና በድህረ ግጭት ዘላቂ ሰላም ስለማስፈን የተጠና ጥናት እንደሚያመላክተው፤ ከ1945 እስከ 2009 ድረስ የእርስ በእርስ ግጭቶችን ካስተናገዱ 103 ሀገራት የእርስ በርስ ግጭት ዳግም እንዳያገረሽ ማድረግ የቻሉት 44 ሀገራት ብቻ ናቸው።

የእርስ በርስ ግጭት ካስተናገዱት ሀገራት መካከል 59 ሀገራት ቢያንስ አንድ ጊዜ ዳግም የእርስ በርስ ግጭቶችን አስተናግደዋል። ይህም ማለት በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የእርስ በርስ ግጭትን ካስተናገዱ ሀገራት ውስጥ 57 በመቶ የሚሆኑት ቢያንስ አንድ ጊዜ ዳግም ወደ እርስ በርስ ግጭት ገብተዋል ማለት ነው።

በተለይም ከእ.አ.አ 2003 ወዲህ በዓለም ላይ የተከሰቱ አብዛኞቹ የእርስ በርስ ግጭቶች የቀደሙ የእርስ በርስ ጦርነቶች ቅጥያ ሆነው ተገኝተዋል። በ21ኛ ክፍለ ዘመን ከተቀሰቀሱ የእርስ በርስ ግጭቶች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት ቀደም ባሉት ዓመታት የእርስ በርስ ግጭቶችን ባስተናገዱ ሀገራት ውስጥ የተፈጠሩ ናቸው።

ጥናቱ በተጨባጭ እንዳመለከተው፤ ከግጭት በኋላ የሚገኝ ሰላም ከፍተኛ እንክብካቤ የሚሻ ፤ግጭቶች የፈጠሩትን ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት በቃ የሚያሰኝ ከልብ የሆነ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ፤ይህንንም ዕለት ተዕለት በተጨባጭ በተግባር ማሳየትን የሚሻ ነው።

በተለይም እንደኛ ያሉ ድህነትን አሸንፎ ለመውጣት አዲስ በሆነ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች ፤ የድህነታቸውም ሆነ የኋላ ቀርነታቸው ምንጭ ግጭቶች ከመሆናቸው አንጻር፤ ግጭቶችን በተቻለ መጠን በውይይት የመፍታት አዲስ የፖለቲካ ባህል መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። ይህንን መፍጠር አለመቻል እንደ ሃገር በቀጣይ በሚኖራቸው እጣ ፈንታ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽእኖ ቀላል አይደለም።

አሁን ባለው ዓለም አቀፍ እውነታ ድህነት ለአንድ ሀገርና ሕዝብ የቱን ያህል ፈተና እንደሆነ፤ይህንን ፈተና አሸንፎ ለማለፍ የሚደረግ ጥረት በራሱ ምን ያህል እልህ አስጨራሽ ትግል እንደሚጠይቅ ያለፉት ዓመታት ተሞክሯችን በተጨባጭ ያሳየን ነው።

የራሳችንን እጣ ፈንታ በራሳችን ለመወሰን የጀመርነውን ሀገራዊ ንቅናቄ /ለውጥ / ተደማምጠን ማስቀጠል አለመቻላችን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለን ዛሬ ላይ ከፍ ባለ ቁጭት ልናስታውሰውና ልንዘክረው ይገባል። የትናንቱ ስህተታችን ከግጭት ነፃ የሆነች ሀገርና ትውልድ መፍጠር የሚያስችል ዕድል አድርገን ልንወስደውም ያስፈልጋል።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ በፕሪቶሪያ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ፈጥኖ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ያለ ወትዋች ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል፤ ከመጠባበቅ ወጥቶ ከጊዜ ቀድሞ መሄድን ፤ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠርንም ይፈልጋል።

የሰላም ስምምነቱ ህገመንግስቱን ፣ ህገመንግስታዊ ስርአቱን እና ብሄራዊ ጥቅምን መሰረት ያደረገ፤ ከዚያም በላይ አሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ ለመላው ሕዝባችን እፎይታ የፈጠረ ነው ይህን የሕዝባችንን ስሜት በተሻለ መልኩ አስቀጥሎ ለመሄድ ከፍ ያለ ቁርጠኝነት ይጠይቃል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ መንግስት ከፍተኛ የልዑካን ቡድኑን ወደ መቀሌ ከመላክ ጀምሮ ፣ በሰላም ስምምነቱ የድርጊት መርሀ ግብር ውስጥ ያልተካተቱ፤ ነገር ግን የበለጠ መተማመንን በመፍጠር የተገኘውን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ እየሄደበት ያለው መንገድ የሚበረታታና ምስጋና የሚቸረው ነው።

የሰላም ስምምነቱ ለትግራይ ሕዝብ ይዞለት ከመጣው እፎይታ አንጻር ፣ ሕወሓት ስምምነቱ ዘላቂ እንዲሆን እየሄደበት ያለው መንገድ ተስፋ ሰጪ ቢሆንም፣ መንግስት እያደረገ እንዳለው ከጊዜና ከቅድመ ሁኔታ አጥር እየወጣ መተማመንን የሚፈጥሩና የሚያጠናክሩ ተግባራትን እውን ማድረግ ይጠበቅበታል።

ይህን ማድረግ የተጀመረውን ሰላም ጠብቆ ከማስቀጠል ባለፈ፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ዋጋ እየተከፈለበት ያለው አዲሱ ሃገራዊ የፖለቲካ ባህል ችግሮችን በንግግርና በውይይት የመፍታት አቅም እንዲገዛ የተሻለ እድል የሚፈጥርም ጭምር ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## እንክብካቤ የሚሻው የድህረ- ግጭት ሰላም

**መሳኩ ኤሮሴ**

ከታሪክ መረዳት እንደምንችለው ሀገራት አንድ ጊዜ እርስ በርስ ግጭት ካጋጠማቸው በኋላ ተጨማሪ እርስ በርስ ግጭቶችን የማስተናገድ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በሰላም ድርድር ያልተቋጩ የእርስ በእርስ ግጭቶችን እጅግ አሳሳቢ ከሚያደርጋቸው ምክንያች አንዱ ግጭቶቹ ከቆሙ በኋላ ዳግም የማገርሸት እድል መኖሩ ነው።

እ.አ.አ በ2010 በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ ግንኙነትና የፓሲፊክ ጥናት የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ባልደረባ የሆኑት በርባራ ዋልተር ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ስለ እርስ በርስ ግጭቶች ማገርሸት እና በድህረ ግጭት ዘላቂ ሰላም ስለማስፈን ያጠኑት ጥናት እንደሚያመላክተው፤ ከ1945 እስከ 2009 ድረስ የእርስ በእርስ ግጭቶችን ካስተናገዱ 103 ሀገራት የእርስ በርስ ግጭት ዳግም እንዳያገረሽ ማድረግ የቻሉት 44 ሀገራት ብቻ ናቸው።

የእርስ በርስ ግጭት ካስተናገዱት ሀገራት መካከል 59 ሀገራት ቢያንስ አንድ ጊዜ ዳግም የእርስ በርስ ግጭቶችን አስተናግደዋል። ይህም ማለት በነዚህ ዓመታት ውስጥ የእርስ በርስ ግጭትን ካስተናገዱ ሀገራት ውስጥ 57 በመቶ የሚሆኑት ቢያንስ አንድ ጊዜ ዳግም ወደ እርስ በርስ ግጭት ገብተዋል ማለት ነው። ይህ አሃዝ እንደሚያሳየው ሀገራት አንድ ጊዜ የእርስ በርስ ግጭትን ካስተናገዱ በኋላ በቀላሉ ከእርስ በርስ ግጭቶች አዙሪት ለመውጣት እንደሚያዳግታቸው ነው።

በተለይም ከእ.አ.አ 2003 ወዲህ በዓለም ላይ የተከሰቱ አብዛኞቹ የእርስ በርስ ግጭቶች የቀደሙ የእርስ በርስ ጦርነቶች ቅጥያ ሆነው እናገኛቸዋለን። በ21ኛ ክፍለ ዘመን ከተቀሰቀሱ እርስ በርስ ግጭቶች ውስጥ 90 በመቶ የሚሆኑት ቀደም ባሉት ዓመታት የእርስ በርስ ግጭቶችን ባስተናገዱ ሀገራት ውስጥ የተፈጠሩ ሲሆኑ 10 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ቀደም ባሉ ዓመታት እርስ በርስ ግጭቶችን ባላስተናገዱ ሀገራት ውስጥ የተከሰቱ ናቸው።

ከእርስ በርስ ግጭቶች ጋር ተያይዞ ያለው ችግር አዳዲስ እርስ በርስ ችግሮች እንዳይፈጠሩ የመከላከል ብቻ ሳይሆን ነባር ግጭቶች ዳግም በማያገረሽ መልኩ እልባት ያለመስጠት ችግር መሆኑን እላይ ከተጠቀሱት አሃዞች መገንዘብ እንችላለን። ሀገራት ከእርስ በርስ ግጭት እንዳይወጡ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ግጭቱን በሀቀኛ የሰላም ድርድር የማይቋጭ ከሆነ ሀገራት የግጭት አዙሪት ውስጥ የመቆየት እድላቸው ይሰፋል።

ኢትዮጵያ ላለፉት ሁለት ዓመታት እጅግ አውዳሚ የእርስ በርስ ግጭቶችን አስተናግዳለች። በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተቀሰቀሰው ግጭት ሀገሪቱ ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሏታል። ብዙዎች ውድ ህይወታቸውን አጥተዋል። ብዙዎች አካላቸውን አጥተዋል። በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከቀዬቸው ተፈናቅለዋል። ብዙ ንብረቶች ወድመዋል። ብዙ ዋጋ ከተከፈለ በኋላም ቢሆን ካለፈው ትምህርት በመውሰድ የእርስ በርስ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በፕሪቶሪያ እና በናይሮቢ የተደረሱ የሰላም ስምምነቶችን ተከትሎ ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማየት ጀምረናል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተውን ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት የሰላም ድርድር እንደ ዋና አማራጭ መወሰዱ ሀገሪቱን ከግጭት አዙሪት ለማውጣት መሰረት እንደሚሆን ተስፋ ተጥሎበታል። በግጭቱ ሁሉም ወገን ተጎድቷል። በሰላም ስምምነቱ ደግሞ ሁሉም ወገን አሸናፊ ነው። ይህ መሆኑ በቀጣይ በቂም ለዳግም ግጭት የሚነሳ ሀይል እንዳይኖር እድል የሚጠብ ነው። ሀገሪቱ አሸናፊ በምትሆንበት መልኩ በንግግር እና በድርድር ለመቋጨት የተደረገው ጥረት ኢትዮጵያዊ ወንድማማችነት አደጋ ውስጥ እንዳይወድቅ መልካም መሰረት የሚሆን ነው።

ከዚያ ባሻገር ሁለቱም አካላት የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ህገ መንግስቱን ለማክበርና ለህግ የበላይነት መከበር ቁርጠኝነታቸውን ማሳየታቸው ግጭቱ ዳግም የማገርሸት እድሉን የሚያጠብ ነው። ከግጭት አዙሪት በዘላቂነት ለመውጣት የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን ከሚደረገው ርብርብ ባሻገር ጠንካራ የፖለቲካ ተቋማትን መገንባት እና የበለጠ እምነት የሚጣልበት የመንግስት መዋቅሮችን መገንባት የሰላም ስምምነቱን ለመተግበር እና ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ እጅግ ወሳኝ ናቸው።

ድህነት እና የመንግስት አቅም ማነስ የእርስ በርስ ግጭቶች እንዲያገረሹ የሚኖረው አስተዋጽኦ ቀላል የማይባል ሚና ይጫወታሉ። ድህነት እና የመንግስት አቅም ማነስ በዓለማችን ከሚስተዋሉ የእርስ በርስ ግጭቶች ጀርባ ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

በመሆኑም ሀገሪቱን ከድህነት ለማስወጣት እና ወደ ብልጽግና ለማሻገር በሚደረገው ርብርብ ውስጥ ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት። ከዚህ ጎን ለጎን ጠንካራ የመንግስት ተቋማትን ለመገንባት በትኩረት መሰራት አለበት። እነዚህ ተቋማት በቀጣይ አለመግባባቶች ወደ ግጭት ሳያመሩ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን መወጣት መቻል አለባቸው።

የኢኮኖሚ ብልጽግና እውን ማድረግ እና ጠንካራ የመንግስት ተቋማትን መገንባት ብቻቸውን ግጭቶችን ሊያስወግዱ አይችሉም። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ድህነት እና የመንግስት አቅም ማነስ በራሳቸው እርስ በርስ ግጭቶች ዳግም እንዲያገረሹ ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም። ከሁሉ በላይ ተፋላሚ ወገኖች ግጭቱን ለማቆም ቁርጠኝነት ማጣት የእርስ በርስ ግጭቶች ዳግም እንዲያገረሹ ከፍተኛውን ሚና ይጫወታሉ። በተለይም ሀገርን የሚያስተዳድር መንግስት ቁርጠኝነት የአንበሳውን ድርሻ ይወጣል።

የኢትዮጵያ መንግስት ሰላም ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ግጭትን ለማቆም እና ዘላቂ ሰላም ለማስፈን እያሳየ ያለው ቁርጠኝነት እጅግ የሚያስደስት ነው። መሰረታዊ አገልግሎቶችን ዳግም ወደ ስራ ማስገባት፣ ሰብዓዊ እርዳታዎች በተሳለጠ መልኩ እንዲዳረሱ በማድረግ ረገድ እየተደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው። በዚህ ረገድ ያለው መልካም ጅምር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

የሕወሓት አመራሮችም በበኩላቸው ግጭቱ በሰላም እንዲፈታ እና የሰላም ስምምነቱ መሬት ላይ እንዲወርድ እያደረጉት ያለው ጥረት ይበል የሚያሰኝ ነው። ይህም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው። ሁለቱም ወገኖች የታየውን የድህረ ግጭት ሰላም መንከባከብ አለባቸው። ከሁለቱ ተደራዳሪ ወገኖች በተጨማሪ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰላም ዘብ መቆም አለበት። ግጭትን ዳግም ለመቀስቀስ ጥረት ለሚያደርጉ አካላት ጆሮ መስጠት የለበትም።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ልዩነታችንን የቱ ጋ ነበር ያቆምነው

በተደጋጋሚ በዚሁ ጋዜጣ ላይ እንደገለጽሁት ሀገር ሲወረር ፤ ሉዓላዊነት ሲደፈር ልዩነታችንን ትተን ቀፎው እንደተነካ ንብ በአንድነት መቆማችንና መትመማችን የሚገባ ቢሆንም ፤ ወረራንና ጥቃትን እየጠበቅን አንድ የምንሆነው የታሪክ ልምምድ ምቾት አይሰጠኝም። አንድ ለመሆን ሁልጊዜ መወረርና መደፈር አለብን ወይ የሚል ጥያቄ ያጭርብኛል። በሰላሙ ጊዜ ለምን ለልማት ለለውጥ በአንድነት አንነሳም ? ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ በአንድነት ለመቆም ለምን እግራችንን እንጎትታለን። የሰሜን ዕዝ ከጀርባው መወጋቱና ጥቃቱ በአንድነት እንድንቆም አድርጎናል። የሰላም ስምምነቱ የጦርነቱን ያህል በአንድነት ለምን አላቆመንም።

በነገራችን ይሄ አባዜ እኔንም ይመለከታል። በረባ ባረባው ልዩነት ልዩነት እያለኝ ነው። ወቀሳው እኔንም ይመለከታል ለማለት ነው። ዛሬ ተመልሰን " ልዩነታችንን የቱ ጋ ነበር ያቆምነው ? " ብለን በይደር ወደአቆየነው የልዩነትና የጥላቻ አዙሪት የምንመለስ ከሆነ ለዚህ ሲባል ወረራንና ጦርነትን የሚሰራ፤ ሀገርንና ሕዝብን እረፍት የሚነሳ ተቋም ወይም እንደ አፄ ልብነድንግል መሬትን 40 እየገረፈ ጦርነት አውርድ የሚል ንጉሱ ያስፈልገናል ማለት ነው።

ከሰላም ስምምነቱ ወዲህም"ልዩነታችንን የቱ ጋ ነበር ያቆምነው ?" ብሎ ወደ ቀደመው ሴራው ፣ ውዝግቡና ብሽሽቁ ተመልሷል። ተቃዋሚው ፣ ዩቲውበሩና አክቲቪስቱ ብቻ አይደለም በራሱ በብልጽግና ውስጥ ያለ አመራር ጭምር "ልዩነታችንን የቱ ጋ ነበር ያቆምነው ?"ብሎ እንካ ስላንትያውንና ሴራ መጎንቆሉን ተቀላቅሏል። ለዚህ አንዱ ምክንያት የተጣባን ክፉ አባዜ ነው ።

በጦርነት ጊዜ ዳር እስከ ዳር በአንድነት አቁሞን ሰላም ሲሆን ደግሞ ወደ ቀደመው ልዩነትና ጥላቻ የሚዘፍቀን ክፉ አባዜ። የአባዜው መነሻ ምን እንደሆነ ግን ራሱን የቻለ ጥናት ይፈልጋል። ሌላው ስለሰላም ስምምነቱ የሚነዙ ብዥታዎችን በወቅቱ ለማጥራት መንግስትም ሚዲያዎቹም እግራቸውን መጎተታቸው የሰላም ስምምነቱን ለሴራ ትንተናና ሀሰተኛ መረጃ ስለዳረገው "ልዩነታችን የቱ ጋ ነበር የቆመው፤"ብሎ ካቆመበት እንዲቀጥል አድርጎታል።

ሌላው ከዚህ ወገንም ሆነ ከዚያ ሀገር ሰላም ሲሆንና ሕዝብ አንድ ሲሆን የሚያባባቸው እኩያን እና የልዩነትና የግጭት ነጋዴዎች ነጋ ጠባ ልዩነትንና ግጭትን የሚፈጥሩ አጀንዳዎችን ስለሚጎነቁሉ ነው። እነዚህ እኩያን በገዢው ፓርቲ ብልጽግና ሳይቀር መኖራቸው ችግሩን አባብሶታል። በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ለተፈጠረው ውዥንብርና ሁከት ራሱ የብልጽግና አመራር እጁ እንደነበረበት በአደባባይ ተነግሯል ። በሰላም ስምምነቱ ላይ ከሚነዙ ውዥንብሮችና አሉባልታዎች ጀርባም ይሄው አመራር አለበት። ዛሬም ብልጽግና መዋቅሩን መፈተሽና ማጽዳት አለበት የሚባለው ለዚህ ነው። ከሁሉም በላይ በተደጋጋሚ እያገረሹ ወደ ልዩነትና ጥላቻ መልሰው የሚዘፍቁን የታሪክ ዕዳዎችና የፈጠራ ትርክቶችን በማያዳግም ሁኔታ በሀገራዊ ምክክሩ እስኪቀረፉ በሚያሳዝን ሁኔታ አብረውን ይኖራሉ።

ኢትዮጵያውያን ከሰላም ጊዜ ይልቅ በጦርነት ጊዜ አንድነታቸው ይበልጥ እንደሚጠነክር በሰሞኑ የሕግ የበላይነትና የህልውና ዘመቻ ፤ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት፤ በሶማሊያ የሲያድባሬ ወረራ ፤ በጣሊያን ሁለተኛ ወረራ፤ በአድዋ ጦርነት ፤ ወዘተረፈ ተመልክተናል።የታሪክ ዳናዎቻችን ሺህ አመታት ወደኋላ ተመልሰን ብንከተል ሀቁ ከዚህ የተለየ አይሆንም።በአብዛኛው በችግር በተለይ በጦርነት ጊዜ የማንኛውም ሀገር ዜጋ ልዩነቱን ወደጎን ብሎ በአንድነት ከባንዲራው ከመሪው ጀርባ ይሰለፋል። ይሁንና ሰላም ሲሆን ወደጎን ወዳቆየው ቁርሾና ልዩነት ይመለሳል ማለት አይደለም።

ሆኖም በመንግስት እንዝህላልነት፣ ከፋፍሎ ለመግዛትና ስልጣን ላይ ለመቆየት ካለው ፍላጎት እና የሕዝቡን አንድነት የሚያዘልቁና የሚያጸኑ ስትራቴጂካዊ ተግባራትን ባለማከናወኑ ፤ በልሒቃን በተለይ በፖለቲካ ልሒቃን ስውር ፍላጎት የተነሳ ፤ በመደበኛና በማህበራዊ ሚዲያ በሚከሰቱ መጓተቶችና ጽንፍ ረገጥ ሚዲያዎች ሳቢያ ፤ ወዘተረፈ የሀገርና የሕዝብ አንድነት ወደ ኋላ ሊንሸራተት ይችላል። በአንጻሩ እነዚህ አካላት ወይም ተቋማት በቅንጅት ለአንድነት ከተነሱ ሀገራዊ አንድነቱን እንደ ብረት እንደሚያጠነክሩት የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ።

የንጉስ ምኒልክ ወደዙፋኑ መቃረብ ያስደሰተው የጣሊያን ወኪል ፔትሮ ኢንቶኔል ግንኙነቱን በፊርማ ለማረጋገጥ ሚያዝያ መገባደጃ ላይ በ1881 ዓ.ም ውጫሌ ላይ የሁለትዮሽ ስምምነት ለመፈራረም በቃ ። ዳሩ ግን ውሎ ሳያድር የስምምነቱ አንቀፅ 17 ውዝግብ አስነሳ። በዚህ አንቀፅ የጣሊያንኛ ቅጅ መሰረት ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነቷን የምታደርገው በጣሊያን በኩል እንደሆነ የሚያስገድድ መሆኑ በተዘዋዋሪ ሀገሪቱን በጣሊያን ሞግዚትነት የምትተዳደር ያደርጋታል።

የአማርኛው ቅጅ ግን የውጭ ግንኙነት ማድረግ ትችላለች ይላል። በስምምነቱ አንቀፅ 19 ላይ የአማርኛና የጣሊያንኛ ቅጅዎች እኩል ተቀባይነት እንዳላቸው መደንገጉ አለመግባባቱን አካረረው ። በ1887 ዓ.ም በወርሀ መስከረም በገበያ ቀን ቅዳሜ አፄ ምኒልክ ታሪካዊውን የ " ወረኢሉን " ክተት አዋጅ አስነገሩ። " ...ሀገርንና ሃይማኖት የሚያጠፉ ጠላት ባሕር ተሻግሮ መጥቷል። እኔም የአገሬ ሰው መድከሙን አይቼ ብታገሰውም ፤ እያለፍ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር ፤ አሁን ግን በእግዚአብሔር እርዳታ አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም።

ያገሬ ሰው ጉልበት ያለህ ተከተለኝ፤ ጉልበት የሌለህ በጸሎትህ እርዳኝ ፤ ..." አዋጁን ተከትሎ በአፄ ምኒልክ አዝማችነት ፣ ከመላው ሀገሪቱ በከተቱት መኳንንትና መሳፍንት ባለሟልነት ከ100ሺህ በላይ ወዶ ገብ የገበሬ ጦር እና 29ሺ ፈረሰኞች በኢትዮጵያዊ አንድነት ፣ ጀግንነት ፣ ቆራጥነት ፣ አልበገር ባይነት ፤ ዳርድንበሩን ፣ ሉዓላዊነቱን ሊያስከብር ቀፎው እንደተነካ ንብ ወደ ሰሜን ተመመ። በዚህም ታላቁ ፣ አኩሪውና አንጸባራቂው የሰው ልጆች በተለይ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ድል የሆነው አድዋ እውን ሊሆን ችሏል።

ድህረ አድዋ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አንድነትን ከመፍጠሩ ባሻገር ሀገሪቱን በወቅቱ ከነበረው ቴክኖሎጂ ጋር እንድትተዋወቅ በር ከፍቶላታል። ድሉ ያስገኘው እውቅና እና ክብር ከውጭ ሀገራት ጋር ሰፊ ግንኙነት እንዲመሰረት ረድቷል። ይህን ተከትሎ ለዘመናዊ አሰራርና አስተዳደር እርሾ የሆኑ ተግባራት እንዲከናወኑም አስችሏል። ከዚህ ባሻገር በጭቆና ቀንበር ይማቅቁ የነበሩ የሰው ልጆችን በተለይ ጥቁሮችን ለጸረ ጭቆና ትግል ከማነሳሳቱ ባሻገር።

ለፓን አፍሪካኒዝም ፣ ለብላክ ኮንሸየስ ፣ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት/ ለአፍሪካ ሕብረትና ሌሎች ንቅናቄዎች መሰረት በመሆን አገልግሏል። በሀገር ውስጥ ግን የቅድመም ሆነ ድህረ አድዋን አንድነት ማዝለቅ ፣ ማጥለቅና ማስፋት ላይ ውስንነት መኖሩን ከንጉሱ ሞትና ከልጅ እያሱ መምጣት በኋላ የተፈጠሩ ልዩነቶችን በአብነት ማንሳት ይቻላል። ከዚህ በላይ ለመሔስ ግን ዘመነ ኋዴነት / ኮንቴምፓራሪነስ/ ይገድበኛል።

> **በጦርነት ጊዜ ዳር እስከ ዳር በአንድነት አቁሞን ሰላም ሲሆን ደግሞ ወደ ቀደመው ልዩነትና ጥላቻ የሚዘፍቀን ክፉ አባዜ። የአባዜው መነሻ ምን እንደሆነ ግን ራሱን የቻለ ጥናት ይፈልጋል**

በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ኢትዮጵያውያን ምንም እንኳ እንደ አድዋው ባይሆንም ወረራውን ለመቀልበስ ዳር እስከ ዳር በአንድነት ተነቃንቋል። ሆኖም በተፈጠሩ ወታደራዊ ስህተቶች እና ጣሊያን ዘመናዊና የኬሚካል ጦር መሳሪያ እስከአፍንጫው ታጥቆ ስለነበር ጦሩ ሊፈታና ጃንሆይም መንግስታቸውን ይዘው ወደ እንግሊዝ ሊሰደዱ መግፍኤ ሆኗል። ያፈገፈገው ጦርና አርበኛ እንደገና ተደራጅቶ፤ ጣሊያን የቆየባቸውን አምስት አመታት ሲዖል አድርጎበታል።

በመጨረሻም በእንግሊዝ ድጋፍና በጀግኖች ተጋድሎ ፋሽስት ጣሊያን ተጠራርጎ ሊወጣ ችሏል ። ከስደት የተመለሰው የግርማዊነታቸው መንግስት አጋጣሚውን በመጠቀም የተፈጠረውን አንድነት ከማጠናከር ከማዝለቅ ይልቅ ፤ በዱር ገደሉ ከወራሪው ጋር እየተዋደቀ ሀገር ያቆየውን አርበኛ ከመሾም ከመሸለም ይልቅ በአምስት አመቱ የጣሊያን ቆይታ ለጣሊያን አድረው ሀገር የከዱ ባንዳዎችን በመሾማቸው እና በመንግስታቸውም ለውጥና ማሻሻያ ያደርጋሉ ተብሎ ሲጠበቅ በዛው በመቀጠላቸው መጨረሻቸው እንዳያምር ከማድረጉ ባሻገር ሀገሪቷንና ሕዝቡን ለወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እና ዛሬ ለምንገኝበት ምስቅልቅል ዳርጓታል።

ደርግ ወደ ስልጣን እንደመጣ መሬት ላራሹን በማወጅ እና ጊዜያዊ ማሻሻያ በማድረግ ያገኘውን ተቀባይነት ማጣት በጀመረበት ሰዓት ፤ በእብሪተኛው የወቅቱ የሶማሊያ ገዢ ዚያድባሬ ታላቋን ሶማሊያ እመሰርታለሁ በሚል የቀን ቅዠት ፤ የኢትዮጵያ አንድነት በውስጥ ተቃውሞና በሻቢያ የትጥቅ ትግል ተዳክሟል በሚል የተሳሳተ ግምገማ በተወሰደ ውሳኔ የሀገራችንን ድንበር ጥሶ እስከ መሀል ሀገር በወረረን ጊዜ መላው ኢትዮጵያዊ ከየማዕዘናቱ የሀገሩን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነቱን ለማስከበር እንደ ንብ ተመመ። በጥቂት ወራት ወታደራዊ ስልጠና የእብሪተኛውን የዚያድባሬ ጦር አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት የግዛት አንድነቷን አስከብሯል።

ይሁንና ደርግ ይህን ሀገራዊ መነሳሳትና አንድነት ለብሔራዊ መግባባትና እርቅ ከመጠቀም ይልቅ ጠመንጃ ወደ ማምለክና ልዩነቱን ሁሉ በኃይል ጸጥ ለማድረግ በመንቀሳቀሱ መጨረሻው ምን እንደነበርና እርሱም ሀገሪቱን ለጠባቡና ቂመኛው ሕወሓት አሳልፎ በመስጠት ለውርደት ዳርጓታል። የሚያሳዝነው በእግሩ የተተካው አገዛዝ ከደርግ ውድቀትም ሆነ ከራሱ ስህተት ለመማር ዝግጁ አለመሆኑ መጨረሻው የሽንፈት ከሉን መከናነብ ሆኗል።

ከኤርትራ ጋር በድንበር የተነሳ ወደ ጦርነት ሲገባ፤ የሀገር ሉዓላዊነት ለአደጋ ሲጋለጥ፤ ሀገር ሲወረር፤ ኢትዮጵያውያን ዳር እስከዳር በነበረው ከፋፍሎ የመግዛት መርህ ፤ አድሎአዊና ኢፍትሐዊ በሆነ አገዛዙ ፤ በአፈናውና በጭቆናው ፤ በኤርትራ መገንጠል በነበረው ወራዳ ሚና ፤ አይን ባወጣው ዘረፋው ፤ ወዘተረፈ የተከፉና ያዘኑ ቢሆንም ከአገዛዙ ጋር የነበራቸውን የማይታረቅ ልዩነት አቆይተው ከጎኑ ተሰልፈዋል ። በነቂስ ተመዋል።

በከፍተኛ መስዋዕትነት የሀገር ዳርድንበርና ሉዓላዊት ወደነበረበት ተመልሷል። ሆኖም አገዛዙ ይህን ሀገራዊ አንድነት ለጊዜያዊ ጥቅም እንጂ ለዘላቂ ሀገራዊ መግባባት ፣ መቀባበልና መቀራረብ ስለማይፈልገው ልጆቻቸውን ያጡ ወላጆች እንባ ሳይደርቅ ወደለመደው ከፋፍለህ ግዛው ፣ አፈናውና አድልዎ ተመለሰ ። ይህን መልካም አጋጣሚ ለሀገራዊ አንድነት ፣ ለብሔራዊ እርቅ ፣ ለለውጥና ለሪፎርም ቢጠቀምበት ኑሮ እንዲያ መውጫው ባልጠፋው፤ ማጣፊያው ባላጠረው።

### እንደ መውጫ

የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትርና የመንግስታቸውን የአመራር ጥበብና ብቃት እንዲሁም ተቋማት በእርግጥ እየተገነቡ መሆኑን በመከላከያ ሰራዊት ግዳጅን የመፈጸም ብቃትና ጀግንነት አረጋግጠናል። በድሉ ከመፎከርና ከመሸለል ይልቅ በሰላም ስምምነት እንዲቋጭ የተሄደበት ርቀት የፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ የአመራር ብስለት የተስተዋለበት ነው። ይህን ተከትሎ በሀገሪቱ የተፈጠረውን መነቃቃትና አንድነት መንግስት ፣ ልሒቃን ፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ መገናኛ ብዙኃን ፣ አክቲቪስቶች ግለቱን ጠብቆ በማስቀጠል ለዘላቂ አንድነትና ብሔራዊ መግባባት መሰረት መጣልና ተቋማዊ ማድረግ ሲጠበቅባችው እያስተዋልን ያለነው ግን ለየቅል ነው።

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት እንዳለው ድሉ ካጎናጸፈን ልዕልና እንዳንወርድ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች ወደ መንደርና ጠባብ አስተሳሰብ ዝቅ እንዳይሉ እንዳሳሰበው፤ በዚህ አንጸባራቂ ድል ማግስት" ልዩነታችን የቱ ጋ ነበር የቆመው !? " ብለን ወደ ቀደመው የሴራ ፖለቲካ፣ አቅላይነት ፣ ጥላቻ ፣ ልዩነት ፣ ጎጠኝነት፣ ምቀኝነት፣ መጠራጠር ፣ ዘረፋ ፣ ወዘተረፈ የምንመለስ ከሆነ ከታሪካችን አልተማርንም። ታጥቦ ጭቃ ፣ አድሮ ቃሪያ ነን ማለት ነውና ወደ ኋላ መመለስና መንሸራተት የለብንም።

ሻሎም ! አሜን።

# ‹‹ኮንትሮባንድ እና ህገ ወጥ ንግድ የማዕድን ዘርፉ ዋነኛ ችግር ነው››

-አቶ ሚሊዮን ማቲዮስ
የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ማዕድን የዓለማችን ትልቁ የገንዘብ ምንጭ ነው። ኢትዮጵያም ከማዕድን በረከት እያገኘች ነው። ሆኖም ካላት የሀብት መጠን አንጻር በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ ሆናለች ማለት አይቻልም። ይሄ ለምን ሆነ? በማዕድን ፈቃድ አሰጣጥ ውስጥ የሚታዩ ጉራማይሌ አሠራሮችና ስለሚስተካከሉበት አግባብ፣ አሁናዊ የማዕድን ዘርፍ ፈተናዎች እና መፃዒ ዕድሎችን በተመለከተ የዝግጅት ክፍላችን ከማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ከአቶ ሚሊዮን ማቲዮስ ጋር ቆይታ አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ያለው አሁናዊ የማዕድን ኢንቨስትመንት ምን ይመስላል?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** 2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት አጠናቀን ሁለተኛው ሩብ ዓመት ውስጥ ነን። በዓመቱ በዋናነት ካቀድናቸው ተግባራት መካከል አንደኛው የማዕድን ዘርፍ በኤክስፖርት የሚጫወተውን ሚና ማሳደግ ነው። ሁለተኛው ገቢ ምርቶችን መተካት ላይ መሥራትና የሥራ ዕድል ፈጠራ ናቸው።

የገቢ ንግድን ከማሳደግ አኳያ ማየት የሚገባው የማዕድን ዘርፍ የረጅም ጊዜ ኢንቨስመንት፣ ትኩረትና እይታ የሚጠይቅ ነው። ከዚህ አኳያ የሚገባውን ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ ያላትን ሃብት መለየትና ሂደቱን ጭምር በብቃት መርቶ ሀገራችን ከዘርፍ መጠቀም የሚገባትን ያህል እንድትጠቀም መስራት ይገባል። ባለፉት ሦስት እና አራት ዓመታት ዘርፉ ለየት ያለ ትኩረት አግኝቷል። ከባህሪው አኳያ የሚፈታተኑት ብዙ ጉዳዮች አሉ። ሆኖም በዘርፉ እምቅ ሃብት አለ። ባለፉት ሦስት ዓመታት ተግዳሮቶች ቢኖሩም ጭላንጭል ተስፋዎች አሉ።

ተኪ ምርቶችን ስንወስድ በማዕድን ሚነስቴር ሥር መሠረታዊ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ አለ። በየዓመቱ አንድ ቢሊዮን ዶላር ወጪ በማድረግ ብረት ከውጭ ያስገባል። 40 የሚጠጉ የብረት ፋብሪካዎች አሉ። መንግስት በወሰነው ውሳኔ መሰረት ሀገሪቱ ያላትን ውድቅዳቂ ብረታብረት መልሶ ከመጠቀም እና የውጭ ምንዛሪ ከማዳን አኳያ እንዲሁም ምርትን በመተካት ረገድ የተጀመረው ሥራ፤ በያዝነውና በሚቀጥለው ዓመት ኢንዱስትሪዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያግዝ ይሆናል።

የገንዘብ ሚኒስቴር አጠቃላይ ሂደቱን ያስተባብራል። ፋብሪካዎች ደግሞ ተረክበው ሥራ ላይ እንዲያውሉ ማዕድን ሚኒስቴር ይከታተላል። ይህ አንዱ ከተኪ ምርት አኳያ ትልቅ ሥራ ነው። የድንጋይ ከሰልን በተመለከተ በየዓመቱ 300 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ታደርጋለች። ይሁንና ኢትዮጵያ ለዘመናት ብትጠቀም የማያልቅ የድንጋይ ከሠል ሃብት አላት። ይህንንም በተወሰነ ደረጃ የማቃጠል አቅም በማሳደግ ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሠል መተካት ይቻላል። በመሆኑም ተኪ ምርትን በሀገር ውስጥ በመተካት ረገድ ከስትራቴጂክ እቅድ አኳያ በትክክለኛ መስመር ላይ ነን።

ኤክስፖርት ከማሳደግ አኳያም በአነስተኛ ይሁን በከፍተኛ ደረጃ የሚመረቱ ምርቶችን፤ ዋናው ምርት ወርቅ ቢሆንም በቀጣይ ሦስት እና አራት ዓመታት በኢንዱስትሪ ደረጃ የምናለማቸው ትልልቅ ሥራዎች አሉ። እስከዚያ ድረስ በአነስተኛና ባህላዊ መንገድ የሚመረቱና ክልሎች የሚያስተዳድሯቸው ፈቃዶች ምርታቸው እንዲጨምር እየተሰራ ነው። በዚህ ረገድ ግን ፈተናዎችም አሉ። ከኩባንያ አኳያ ትልቁ ወርቅ አምራች ሜድሮክ ነው። ይሁንና በቀጣይ ሦስትና አራት ዓመታት ውስጥ ወደ ሥራ የሚገቡና ከሜድሮክ የሚልቁ ኩባንያዎች በአሁኑ ወቅት በሥራ ሂደት ላይ ናቸው።

ቤኒሻንጉል ላይ ኩርሙክ የሚባለውና በወርቅ ላይ የተሰማራው በጣም ትልቅና ሰፊ ሥራ እየሰራ ነው፤ ለሀገርም ትልቅ ተስፋ ይሰጣል። በጋምቤላ ኢትዮ ማይንስ የሚባል ኩባንያ በወራት ዕድሜ ወደ ሥራ ይገባል ብለን እናስባለን። ከአሁን በኋላ በወርቅ ምርት ከሜድሮክ ተጨማሪ ሌሎች ግዙፍ ኩባንያዎች ይኖሩናል። የውጭ ምንዛሪ በከፍተኛ ደረጃ ያመጣሉ። ለእነዚህም ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ በሩብ ዓመቱ ከክልል መንግስታት ጋር በሰፊው ስንቀሳቀስ ቆይተናል። 35ሺ ዜጎችም የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር በተደረገው የተቋማት ሪፎርም ማዕድን ሚኒስቴር ምን አገኘ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ከሪፎርም አኳያ ሲታይ በዘርፉ ላይ ከዚህ ቀደም ምን ሲባል እንደነበር ማስታወስ ተገቢ ነው። ማዕድን ማለት የሁከትና ግጭት እንጂ የልማት መሰረት አድርጎ አለማየት ነበር። ሆኖም ከአጭር ጊዜ አኳያ የካፒታል ፍላጎት የሚያሟሉ የተፈጥሮ ፀጋ ነው። በዚህ ሀገር ከዘርፉ ሁሉም ይጠቀማል ብሎ ማህበረሰቡ ማሰብ ከቻለ ማዕድን ፀጋ ነው። በዚህም የተጠቀሙና የተለወጡ ሀገራት አድርገውት አሳይተውናል። ስለዚህ ማዕድን የሁከትና ግጭት ሳይሆን የምንለወጥበት ነው። ቦትስዋና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኖርዌይ በቅርቡ ደግሞ ታንዛኒያን ብንመለከት የኢኮኖሚ መሰረታቸውና ዕድገታቸው ማዕድን ሆኗል። ወደ ኋላ ስንሄድ ደግሞ አውስትራሊያ እና ካናዳ የዕድገታቸው መሰረት ማዕድን ነው። ሁልጊዜ የመጥፎ ምሳሌ የሆነችው አፍሪካዊት ሀገር ኮንጎን በመጥቀስ ሀገራችንና መንግስት ትክክለኛ ፖሊሲ ሳይከተሉ ቀርተዋል። በአግባቡ ካልተያዘ የማዕድን ብቻ ሳይሆን የእርሻ መሬትም የሁከትና ግርግር ምንጭ ይሆናል።

ከሪፎርም አኳያ አንዱ ይህን ዕይታ ማስተካከል ነው። ሀገርን የሚቀይር ሃብት በእጅ ይዞ ገና ለገና ሁከትና ግጭት ይፈጠራል ብሎ ሃብት አለመጠቀም መሠረታዊ ስህተት ነው ብለን በመመልከት የስኬታማ ሀገራትን ተሞክሮ ማየት ነበረብን። ማዕድን በጥሬው መሸጥና ወደ ውጭ መላክ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ኢኮኖሚ ወደሚቀጥለው ምዕራፍ እንዲሸጋገር በረጅም ጊዜ ደግሞ የካፒታል ምንጭ እንዲሆን ነው። የውጭ ምንዛሪ ፈተና የምናልፍበት አንዱ የማዕድን ሃብት በመጠቀም ነው። አንዳንድ ሃገራት ችግሮችን ያለፉበት የዜጎቻቸው ፀጉር ሸጠው ነው። ስለዚህ እኛ ሃብታችንን በአግባቡ መጠቀም አለብን። በመሆኑም በሪፎርሙም ቅድሚያ የሰጠነው ዕይታን ማስተካከል ላይ ነው ።

ማዕድን ለብረት ልማት፣ ለኢንዱትሪ ልማት፣ ለማዳበሪያ ልማትና ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ሲሆን ሀገር ትለወጣለች፤ በሚልና የካፒታል ምንጭ መሆን አለበት በሚል የፖለቲካ እይታ እንዲኖር ተደርጓል። ይህ በተወሰኑ ተቋማት ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ እይታውን በማስተካከል ነው። ይህም የተቋማት ፖሊሲና አመለካከት ላይ ተጨባጭ ለውጥ አምጥቷል። በመሆኑም በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ማዕድን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ምሰሶ እንዲሆን ታስቧል ።

**አዲስ ዘመን፡- ከ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅዶች አንዱ ማዕድን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ምሰሶ ማድረግ ነው። ይህን ለማሳካት ሚኒስቴሩ ምን የተለየ አካሄድ ይከተላል?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** በነገራችን ላይ ይህንን መረዳት ወሳኝ ነገር ነው። የኢትዮጵያን ማዕድን ሃብት 30 ከመቶም አላወቅነውም። 70 ከመቶ ዝርዝር ጥናት አልተካሄደበትም። ነገር ግን በሚቀጥሉት 10 ዓመታት የሚለማው ተለይቷል። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ግብርና ማዘመን አለባት፤ የግብርና ትራንስፎርሜሽን እያልን 20 ዓመታት ተጉዘን መጥተናል። ሆኖም በየዓመቱ እስከ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ድረስ ማዳበሪያ ከውጭ እንገዛለን። አሁን ማዕድን የብልፅግናችንና የኢኮኖሚያችን መሰረት ነው ብለናል። ማዳበሪያ ማለት በዋናነት ከአፋር የምንወስደው ፖታሽ እና ሳልፈር፤ ከወለጋ የምንወስደው ሳልፌት እና ኦጋዴን ላይ ያለን ጋዝ በማቀላቀል የሚፈጠር ነው። በዚህ ረገድ 60 ዓመት የሚበቃ ሃብት አለን። በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሆነ ፖታሽ አለን። በመሆኑም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ ማዳበሪያ ካመረተች እንደ ህዳሴ ግድብ የሚታይ ትልቅ ስትራቴጂክ ልማት ነው።

ስለዚህ ማዳበሪያ ማምረት ስትራቴጂክ ግብዓት ማለት ነው። በመሆኑም አንዱ የተሰጠን ተልዕኮ በመካከለኛ ጊዜ ማዳበሪያ ማምረት ነው። የምግብ ዋስትና ችግር አለብን።



ፎቶ፡- እዮብ ተፈሪ

በየዓመቱ ከ20 እስከ 30 ሚሊዮን ህዝባችን ይቸገራል። ስለዚህ የግብርና ዘርፍ ለኢንዱስትሪ ግብዓት አቅራቢና ወደ ውጭ ምርት ለመላክ እንዲችል ወሳኙ ግብዓት የአፈር ማዳበሪያ ነው። እስካሁንም ማምረት ነበረብን ብለን ነው የምናስበው።

ሁለተኛው ብረት ነው። አንድ ሀገር በኢንዱስትሪ ለመልማት በሚያስብበት ጊዜ ወሳኙ ግብዓት ብረት ነው። የኢንዱስትሪ አብዮት ማለት ብረትና ከብረት ጋር ተይይዞ ያለው በመካኒካል ኢንጂነሪንግ የመጣ የአሰራር ለውጥ ነው። ስለዚህ በወሣኝነት የወደፊት ተስፋ አለው የሚባለው በብረት የለማ ሀገር ነው። ብዙ ሀገራት በሀገራቸው የብረት ማዕድን ባይኖር እንኳን በመርከብ ከብራዚል፣ ከደቡብ አፍሪካና ሌሎች ሀገራት አጓጉዘው በዓለም ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆነዋል። ስለዚህ ብረት ማምረት ማለት አንድ ስትራቴጂክ ግንባርን በድል መወጣት ማለት ነው። ለሚቀጥለው ትውልድ ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት መሠረት ይዘናል ማለት ነው።

ኢትዮጵያ ከአንድ ቢሊዮን ቶን በላይ የብረት ማዕድን አላት። ሰቆጣ ላይ ከ600 ሚሊዮን ቶን በላይ ፤ ሸሬ ላይ ከ250 ሚሊዮን ቶን በላይ ፤ መካነ ሠላም ላይ 80 ሚሊዮን ቶን አለን። ወለጋ፣ ጅማ፣ ጉጂ፣ ቦረና ላይ ትልቅ ክምችት አለ። እነዚህ በሚቀጥሉት 10 የስትራቴጂክ ዕቅድ ዓመታት ኢትዮጵያን ወደሌላ ምዕራፍ የሚያሸጋግሩና ትልቅ ሃብት ነው።

አሁን ያሉት ብረት ፋብሪካዎች ከ30 እስከ 40 ይደርሳሉ። እነዚህ ሁሉንም ከውጭ አምጥተው የተለያየ ቅርፅ አውጥተው የሚሸጡ ናቸው። ከአጭር ጊዜ አኳያ እየታሰበ ያለው እነዚህን ፋብሪካዎች እንዲንቀሳቀሱ ነው። ዘላቂ ልማት ከማሰብ አኳያ ኢትዮጵያ ያላትን ብረት ማዕድን ወደ ሥራ ማስገባት አለባት። ይህም ሪፎርሙ ያመጣው መሠረታዊ የፖለቲካ ውሳኔ ነው። ይህም መሰረታዊ በመሆን መንገድ የሀገሪቱን ገፅታ ማሳደግ፣ መለወጥና የመፈብረክ አቅምን ከፍ የሚያደርግ ነው።

ሌላው ደግሞ የጋዝ ልማት ነው። በኦጋዴን ሰባት ትሪሊዮን ኪዩቢክ ፊት የሚሆን ሃብት አላችሁ ተብለን ተረጋግጦልናል (ሰርትፋይ ተደርገናል)። ይህ ባንክ ውስጥ እንዳለ ገንዘብ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። ጋዝ ሲለማ ደግሞ ፔትሮ ኬሚካል አብሮ ይለማል። ከፔትሮ ኬሚካል ደግሞ ብዙ ነገሮች ይመረታሉ። አውሮፓና ራሺያ የገቡበትን ፍጥጫ አይተናል። ይህን ያመጣው ይህ ጋዝ ነው። ስለዚህ እኛ ያለን ጋዝና በተጓዳኝ ያለው ልማት በቀላሉ አይታይም። ማዳበሪያን ከማምረት አኳያ ትልቅ ለውጥ የምናመጣ ሲሆን፤ በእቅድ የሚሠሩ ሥራዎችም ይኖራሉ።

በሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት ከ510 ሺህ ኪሎ ግራም የማያንስ ወርቅ በኩባንያ ደረጃ ይመረታሉ። እነዚህ ኩባንያዎች በቅርቡ ሥራ ይጀምራሉ። ለምሳሌ ጋምቤላ ያለው ኢትዮ ማይንስ በሦስት ወራት ወደ ሥራ ይገባል። በቤንሻንጉል ያለው ኩርሙክ የወርቅ ካምፓኒ ትልቁ አምራች ሲሆን በሚቂጥሉት አምስት ዓመታት ወደ ምርት ይገባል። ሜድሮክም በዚህ አካባቢ እየሠራ ነው። ወለጋ አካባቢም ተመሳሳይ ሥራ አለ። እነዚህ ፍለጋዎች ተጠናቀው ሥራ ላይ ያሉ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ፍለጋ ላይ የተሰማሩ አሉ። ከእነዚህ ተጨማሩ ሃብት ይገኛል።

የ21ኛው ክፍለ ዘመን የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች የሚሰሩባቸውና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች የሚገነቡባቸው ለምሳሌ የንፋስ ኃይል ማመንጫ፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ስልክን ጨምሮ የሚሰሩባቸው ማዕድናት ለአብነትም ማንጋነዝ፣ ኒኬል፣ ሊትየም፣ ቴንታሊየምና ሌሎች የማዕድን ዓይነቶችም በኢትዮጵያ አሉ። የውጭ ኢንቨስተሮችም ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ ነው። እነዚህ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ማዕድናት ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ ውድ የሆኑ የዘመኑ ቴክኖሎጂዎች፣ ድሮንን ጨምሮ ውድ የጦር መሳሪያዎች የሚመረቱባቸው በመሆናቸው ነው። እኛ ደግሞ በተፈጥሮ በእነዚህ የታደልን ነን።

ኢትዮጵያ ካላት የጂኦሎጂ አፈጣጠር አንፃር ስምጥ ሸለቆን ይዞ በአፍሪካ ቀዳሚ የጂኦ ተርማል ኢነርጂ ባለቤት

# ወቅታዊ

ነን። ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፍላጎት እያሳዩ ሲሆን፤ አልምተው ለመሸጥ ውል የገቡም አሉ። በዚሁ ስምጥ ሸለቆ በመዝናኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ መሠማራት የሚፈልጉም አሉ። ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ በርካታ ማዕድን አለን። ለሲሚንቶና ሴራሚክስ የሚውል ግብዓት በሰፊው አለን። እኛ በየዓመቱ በሚሊዮን ዶላር ወጪ እምነበረድ ወደ አገር እናስገባለን። በሀገራችን ግን በስፋትና በጥራት ይገኛል። ኢትዮጵያ ገና የምትገነባ ሀገር ናት። ፈተናዎች ቢኖሩም ኢንቨስተሮችም በስፋት እየገቡበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገሪቱ በማዕድን ዘርፍ የጀመረቻቸው በርካታ ሥራዎች በህብረተሰቡ አመኔታ ያጡና የቅሬታ ምንጭም ነበሩ። ቀደም ሲል ሜቴክ የጀመረው የከሰልና በወርቅ ሳይም የነበረውን ችግር ማስታወስ ይቻላል። ከዚህ ችግር መውጫ መንገድ አለን?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ዘርፉ ላይ መላልሰን ማየት የሚገባን ዘርፉ ከፍተኛ ካፒታል፣ ትዕግስት፣ እውቀትና ቴክኖሎጂ የሚጠይቅ ነው። አንዳንዱ የረጅም ጊዜ እይታና በተግባር ሂደት መማርን የሚጠይቅ ነው። በማዕድን ዘርፍ የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ስናይ የግሉ ዘርፍና ኮርፖሬቶች የሚሰሩት ለትርፍ ነው። የግሉ ዘርፍ ለትርፍ ስለሚሰራ ሁሉንም ይሠራል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው። ስለዚህ መንግስት ጠንክሮ ራሱ ይሠራል። ለምሳሌ ጋዝ በራሱ ሃብት ነው። ነገር ግን ለማልማት በቢሊዮን ዶላር ወጪ ይጠይቃል። ከዚህ አኳያ የሚጠይቀውን ነገር ስላለ በአግባቡ መያዝ ይገባል። ያለን ሃብት በአግባቡ በዓለም አቀፍ ኩባንያ በሳይንሳዊ መንገድ ሲለካ ማልማት የሚፈልግ አካል ይመጣል ማለት ነው። ስለዚህ እኛ ይህ ተሚቶልናል። ለብዙ ጊዜ ሙከራዎች ነበሩ። እነዚያን ምዕራፍ አልፈን ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ምርጫ ላይ ነን።

ማዳበሪያ ላይም ስንመለከት ፍላጎት ነበር። በራሱ ፍላጎት መኖሩ ችግር አይደለም። ግን የተሄደበት መንገድና ከሜቴክ ጋር የነበረው ግንኙነት ችግር ነበረበት። በሀገራችን ማዳበሪያ ለማልማት የሚያስችልን መሠረታዊ ግብዓት በአፋር እና ኦጋዴን በስፋት አለ። አሁን በአዲስ እይታ እየሰራን ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ ተገቢ በመሆኑ በዚያ ልክ ሄደናል። ስለዚህ ከባለፈው ውድቀት በመማር ተገቢውን ሥራ እየሠራን ነው። በዘርፉ መንግስት ብቻውን ያልማ ወይስ የውጭ ባለሃብቶች ይግቡበት የሚለውን ለማወቅም በዓለም አቀፍ ኩባንያ አስጠንተናል። የባለፈውን ስህተት ለማረም የሚያግዙን ሥራዎችን እየሠራን ነው።

በሚኒስቴራችን ስር የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አቋቁመናል። ትልቁ ሥራው ግዙፍና ሀገራዊ ጠቃሜታ ያላቸውን ስራዎችን የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ ለውሳኔ ሰጪ አካል ማቅረብ ነው። አስቀድሞ የነበሩ ጉድለቶችንም ያሟላል። ከባዱን ስራ በሆነ ቦታ መጀመርና ለቀጣይ ሥራ መሰረት መጣል አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገሪቱ ካላት የማዕድን ሃብት አኳያ ይህን ለመምራት የሚችል የሰው ኃይል አላት?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** መሰረታዊ ጥያቄ ነው። ማዕድን ከፍተኛ እውቀትና ካፒታል ይጠይቃል። የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አንዱ ስራው በዘርፉ ላይ ዕውቀት ያለው አካል ማፍራት ነው። በዘርፉ የመጀመሪያ ሥራ ፍለጋ ነው። የእኛ አቅም ደግሞ ውስን ነው። ስለዚህ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ገና ለፍለጋ ወደ ሀገራችን ሲመጡ እየሠራን ልምድ እየተጋራን፤ እውቀት እየቀሰምን ነው። የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዓላማም በዘርፉ ያለውን ቴክኖሎጂና እውቀት ማሳደግ ብሎም ሀብታችንን ማስተዋወቅ ነው።

ሁለተኛው ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየሰራን ነው። አሁን የዩኒቨርሲቲዎች አወቃቀር በመሠረታዊነት ተቀይሯል። እውቀትን ከማዕከል ለማሰራጨት እየተሰራ ነው።

ዩኒቨርሲቲዎች በየአካባቢያቸው ያለውን ፀጋ ማልማት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ተዋቅረዋል። ለምሳሌ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የትኩረት መስኩ አንዱ ማዕድን ላይ ነው። ስለዚህ ወደፊት በክልሉ የማዕድን ሀብት ላይ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በምርምር፣ ተማሪዎችን በማሰልጠንና፣ በፍለጋ፣ ከካምፓኒዎች ጋር ባለው ግንኙነትም ላይ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ይህም ክልሉንና ሀገርን ለመጥቀም ያግዛል። ወለጋ ዩኒቨርሲቲም አንዱ የትኩረት መስክ ማዕድን ነው። ይህም ኢንዱስትሪና ዩኒቨርሲቲዎች ተናበው እንዲሰሩ ያግዛል። በአሶሳና በአጋዴንም በተመሳሳይ እየተሠራ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር፣ ማይኒንግ ኢንጂነሪንግ፣ ፔትሮሊየም ኢንጂነሪንግ፣ በላብራቶሪና በመሳሰሉት ተማሪዎችን ከየክልሉ እየተቀበለ የክልሎችን አቅም ለማሳደግ እያሰለጠነ ነው። የማዕድን ሚኒስቴር አቅም ለማሳደግ የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስልጠናና ወርክሾፕ በማዘጋጀት አቅሙን ከፍ እያደረገ ነው።



**አዲስ ዘመን፡- በማዕድን ዘርፍ በዓለም ላይ እውቅ ካምፓኒዎችን የማሳመን ሥራ እና የማዕድን ዲፕሎማሲ ሥራ ይጠይቃል። በዚህ ላይ ሚኒስቴሩ ምን እየሠራ ነው?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ይህም መሰረታዊ ጥያቄ ነው። እጅ አጣጥፎ በመቀመጥ የሚታሰበውን ማሳካት አይቻልም። ማዕድን በማልማት 150 ዓመት ልምድ ያላቸው እነ አውስትራሊያ፣ ካናዳ እና ደቡብ አፍሪካ ናቸው። በዓመት ሁለት ግዙፍ ኤክስፖዎች አሉ። አንዱ ደቡብ አፍሪካ የሚካሄደው ሲሆን፤ የሀገር መሪዎች፣ የፋይናንስ፣ የኢንሹራንስና የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች በብዛት የሚገኙበት ነው። በዚህ ላይ የሀገር መሪዎች ተገኝተው ኩባንያዎችን ጭምር ያግባባሉ።

ሁለተኛው ደግሞ ካናዳ የሚካሄደው ኤክስፖ ነው። በዚህም ላይ በማዕድን ዘርፍ አሉ የሚባሉ ግዙፍ ካምፓኒዎች በሙሉ ይሳተፋሉ። እነዚህ ግዙፍ ኩባንያዎች ፈቃድ ከወሰዱ በኋላ በስቶክ ማርኬት ላይ ትልቅ ሚና አላቸው፤ እዚህ ገብተው ገቢ ያሰባስባሉ። እኛ ሀገር ገና ስቶክ ማርኬት እየተጀመረ ነው። በዚህ ላይ በሰፊው የምንሰራ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከማዕድን ፈቃድ አሰጣጥ ጋርም በርካታ ቅሬታዎችና ችግሮች ይስተዋላሉ። በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ከፈቃድ አሰጣጡ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ እስካሁን ባለው ሁኔታ የማዕድን ሀገር አይደለችም። ከሪፎርሙ ወዲህ መነቃቃት አለ። የኢትዮጵያ አቅም ውስን ነው። ፈቃድ ላይ ፍለጋ ሲባል ማሰራት ያለብን ለምንነ ነው ። ፍለጋ እስከ 10 ዓመት ሊጠይቅ ይችላል። በተለያዩ ምክንያቶችም ሊሰነካከል ይችላል። ፈቃድ ፍለጋ ሲጠናቀቅ በካምፓኒ በከፍተኛ ደረጃ ለሚሠሩት የማይኒንግ ፈቃድ የሚሰጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው። በአነስተኛ ደረጃ ለሚሰማራው ፈቃድ የሚሰጠው ክልል ነው። ከፍተኛ ደረጃ ለሚያመርቱ ፈቃድ የሚሰጠው በመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች ስለሆነ ግልጽነቱን ማወቅ ቀላል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ግልፅነት የሰፈነበት ከሆነ በየጊዜው በኮንትሮባንድ የሚያዘው ማዕድን ምንጭ ምንድን ነው?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ጥያቄው ከዚህ በላይ ነው፤ ግን መሠራት ያለበት ሲስተሙ ላይ ነው። ሪፎርሙ ሲሠራ የነበሩ አዋጆች፣ ፖሊሶችንና ደንበኞችን በማየትም ጭምር ነው። ይህ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል። የማዕድን ፈቃድ እንዴት ይሰጣል፣ እንዴት ይተዳደራል፣ ፈቃድ ህገ ወጥ ሲሆን እንዴት ይቋረጣል የሚለው ጭምር ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል። ቀደም ሲል የተፈጠረ አቅም አለ። አንዱ የካዳስተር ሲስተም ሲሆን፤ በማዕድን ላይ መሰማራት የሚፈልግ አካል ኦንላይን ሆኖ ከየትኛውም ቦታ ለመሰማራት ፈቃድ የሚጠይቅበት አግባብ ነው። በዚህ ደረጃ ግልፅ ነው። የማዕድን ፈቃድ አስተዳደርና አሰጣጥ ከሙስና እንዲፀዳ አዳዲስ አሰራሮች እየተተገበሩ ነው።

ኮንትሮባንድ እና ህገ ወጥ ንግድ የዘርፉ ዋነኛ ችግር ነው። ማዕድን የኢትዮጵያ ህዝብ ሃብት ነው። ግን አሁን ያለው ፈቃድ አሰጣጥ ላይ አብዛኛው አነስተኛ ፈቃዶች አሉ። በወርቅ ላይ ብናይ 317 ፈቃዶች አሉ፤ እነዚህ በማህበራት የሚመርቱ ናቸው። ኦሮሚያ ክልል 119 ፈቃድ የተቀሩት ደግሞ በአራቱ ክልሎች ሲሆኑ ፈቃድ የሚያገኙት ከክልል ነው። ፌደራል ላይ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ፈቃድ ይወስዳሉ። ከፌደራል የተሰጠው ስድስት አይበልጥም፤ ጨኸቶች ተደበላልቀው መሄድ የለባቸውም። 317 ፈቃዶች የፌደራል መንግስት አይደሉም። ጌጣጌጥ ላይ ወጣቶችንና ማህበራትን አደራጅተው ፈቃድ የሚሰጡት ክልሎች ናቸው። ወደ ፌደራል ሲመጡ ምናልባትም የኤክስፖርት ፈቃድ ለመጠየቅ ነው። ነገር ግን ወደፊት ወርቅን በመሰለ ነገር ላይ ፈቃድ በቀላሉ መስጠት አለበት ወይ የሚለው አጠያያቂ ነው። ይህ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓቱ በተለይም በኤክስፖርት ማዕድናት ላይ በጥንቃቄ መታየት አለበት የሚል አቋም አለን።

317ቱ ፈቃዶች በአነስተኛ እና ባህላዊ መንገድ ለተደራጁ የተሰጡ ናቸው። ግን የሚጠቀሙት ማሽን ከክልል ፈቃድ በላይ ነው። ይህ ቴክኖሎጂ ደግሞ የክልል ሳይሆን የፌደራል መንግስት መሆን አለበት። አዲሱ ሪፎርምና አዋጁም እነዚህን ይመለከታል። በማዕድን ላይ ህገ ወጥነትና ኮንትሮባንድ እየተፈታተነን ነው። ሀገር ከፍተኛ ዋጋ እየከፈለች ነው። ይህን መልክ ማስያዝ ያስፈልጋል፤ መንግስትም ጠንክር ያለ አቋም እያሳየ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገሪቱ ካላት ከፍተኛ የብረት ሃብት አንፃርስ ወደ ምርት ለመቀየር ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተቋቋመበትና ሥራ ተብሎ ከተሰጠን አንዱ ብረት ልማት ነው። ስለዚህ በዚህ ላይ የአዋጭነት ሥራ እየሰራን ነው። ሰቆጣ፣ ሽሬ፣ መካነ ሰላም፣ ወለጋ ላይ ከፍተኛ ሃብት አለን። ከአዋጭነት ጥናቱ አንዱ ያለን የብረት ጥራት ምን ይመስላል የሚለው ሲሆን፤ በግል ደረጃም ፈቃድ ወስደው ጂማ፣ ጉጂ እና ቦረና አካባቢዎች ላይ በፍለጋ ጥሩ የምርመራ ውጤት ያገኙ አሉ። በጋምቤላም በተመሳሳይ እየተሳተፈ የሚገኝ የውጭ ባለሃብት አለ። የግሎቹ በፍጥነት ወደ ኢንዱስትሪ እንደሚገቡ ተስፋ እናደርጋለን። እኛ ብቻ ሳንሆን የግል ባለሃብቶች እየተሳተፉበት ነው። በሀገሪቱ ውስጥ ትልቅ የብረት ፍላጎት አለ። በቀጣይ ለሀገሪቱ ልማት ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ተስፋ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- በጂኦ ተርማል ላይ ምን አዲስ ውጥን አለ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ከአፋር ተነስቶ እስከ ዓባያ ሃይቅ የሚዘልቅ ትልቅ ሃብት አለን። በዚህ ላይ ሥመ-ጥር ኩባንያዎች ገብተው እየሠሩ ሲሆን፤ በቅርበት እንከታተላለን። ወደምርትም እየገቡ ያሉ ሲሆን በቀጣይ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ጂኦ ተርማል ኤሌክትሪክ ኢነርጂ ማምረት ብቻ ሳይሆን ፍል ውሃ በማልማትም ረገድ ትልቅ ፋይዳ አለው። ይህም ወደፊት የቱሪዝም መስህብ ትልቅ የገቢ ምንጭ ይሆናል ብለን እናስባለን። ጥሩ እየሄደ ስለሆነ እንደ ሀገር ተስፋው በጣም ትልቅ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የማዕድን ስፍራዎችና ከአካባቢው ህዝብ ጋር ያለው መስተጋብር የሚመራበት ህጋዊ አግባብ አለ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** አንዱ የማህበረሰብና አካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም ነው። እስካሁን የተከተልነው መንገድ ኢትዮጵያን የማዕድን ሃብት ተጠቃሚ ሀገር አላደረጋትም። በቀጣይ ማንኛውም እንቅስቃሴያችን የዓለም ግዙፍ ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ ጋር ሲሠሩ ማየት ነው። በዚህ አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭና ማኑፋክቸሪንግም እንገነባለን። ማዕድን ስናስብ ለቀጣይ ትውልድም ጭምር በማሰብ የሚተገበር ነው። እኛ ባለን ትንሽ ሥራ ቅሬታዎች የነበሩ ቢሆንም ነገር ግን ትምህርት ስለወሰድን እየተስተካከሉ ይሄዳሉ። ከዚህ በተረፈ እንደ ሀገር በህግ መመራት አለብን። አንድ ኩባንያ ኢትዮጵያ ሲመጣ ህግና ሥርዓት አከብራለሁ ብሎ ነው። ከዚህ ውጭ የጥቅም ክፍፍልን በተመለከተ ከህገ መንግስቱ ጨምሮ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያወጣው ህግ አለ። ይህን ህግ መተግበርና መስራት ይገባል። አንዳንድ ቦታ ላይ ወደ ሥራ በፍጥነት አልተገባም ሲል ህብረተሰቡ ይወቅሳል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች አሉ።

ለምሳሌ ቤንሻንጉል ኩሙርክ ላይ ወደ ሥራ የተገባውና ኩባንያ የተቋቋመው 140ሺ ኪሎ ግራም ወርቅ በጥናት ተለይቶ ነው ። በዚህ ከፍተኛ ኢንቨስትመንትና መዕዋለ ንዋይ በወጣበት ቦታ ላይ ወረራ በመፈፀም፤ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ተሰማርተው እንዲሠሩ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አሉ። እነዚህ በሙሉ ፈፅሞ ተቀባይነት የላቸውም፤ ህግ መከበር አለበት። ሚሊዮን ዶላር የወጣበትን የሥራ ፈቃድ የሰጠው መንግስት ነው። ስለዚህ መሠል ድርጅቶች መዋከብ የለባቸውም። የሀገራችን መልካም ገጽታ፣ የህዝብ ልማት ወዳድነትና ፍላጎት መቅድም አለበት። መንግስትም ይህን ታሳቢ ያደረገ ሥራ ያከናውናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ሳደረጉት ቆይታ እያመሰገንሁ፤ የማሳረጊያ ሐሳብ ካለዎት?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** አመሰግናለሁ። ኢትዮጵያ በአራቱም ማዕዘናት ትልቅ ፀጋ አላት። የካፒታል ፍላጎቷን ከማሟላት አኳያ የማዕድን ሀብቷን መጠቀም ሲሆን፤ይሄ አሁን በጥሩ አግባብ ተይዟል። ስለዚህ የአሁኑ ቀጣዩ ትውልድ ከዚህ መጠቀም አለበት። በቀጣይ አስር ዓመታት ማዕድን ትልቅ ሚና የሚኖረው ሲሆን የሀገራችንን ገጽታንም ስለሚቀይር ህገ ወጦችን ማስቆምና በህጋዊ አግባብ ይህን ሃብት መጠቀም ይጠበቅብናል። መንግስት ለሚያደርገው ጥረትም ህዝባችን አጋዥ መሆን አለበት የሚል ጥሪ ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# ከጦርነት ፅልመት ወደ ተስፋ እየተሸጋገረ ያለው የኮምቦልቻ ኢንቨስትመንት

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ከኮምቦልቻ ሪጆፖሊታን ከተማ አስተዳደር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ኮምቦልቻ ከተማ 1943 ዓ.ም ነው የተቆረቆረችው። ኮምቦልቻ ከተማ በ1965 ዓ.ም ጀምሮ በማስተር ፕላን የምትመራ ዘመናዊ ከተማ ትሆን ዘንድ በብዙዎች ዘንድ ቀልብ ገብታለችና የከተማነት ክብርን ስትጎናጸፍ ጊዜ አልፈጀባትም። በደርግ ዘመነ መንግስትም የቃሉ አውራጃ ዋና ከተማ በመሆን ተወዳጅና ተመራጭ ከተማ በመሆን የመንግስታዊዎቹ የጨርቃጨርቅ፤ እንዲሁም የስጋና የቆዳ እንዲሁም የቢራ ፋብሪካዎችን አስተናግዳ የሥራ ከተማነቷንና ለኢንቨስመንት ምቹ መሆኗን አረጋግጣለች።

እስከ 2012 ዓ.ም በከተማ አስተዳደርነት ስትመራ የቆየችው እና በተለይም የባለሃብቶችን ቀልብ እየሳበች የመጣችው ኮምቦልቻ፤ በዘመናት ጉዞዋ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ተገንብተውባታል። የበርካቶችን ልብ መግዛትና መዋዕለ ነዋያቸውን እንዲያፈስሱ ያደረገችው ኮምቦልቻ ታዲያ 2013 ዓ.ም ላይ ከከተማነት ወደ ሪጆፖሊታን ከተማ አስተዳደር በማደግ የከተማዋን ዕድገትና የሕዝቦቿን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ላይ የምትገኝ ፈጣን ለውጥ እያስመዘገበች ትገኛለች።


የኮምቦልቻ ሪጆፖሊታን ከተማ አስተዳደር 124ነጥብ5 ሄክታር የቆዳ ስፋት ያላት ሲሆን፤ በምስራቅ ቃሉ ወረዳና የደሴ ዙሪያ ወረዳ፤ በደቡብ ቃሉ ወረዳ፤ በምዕራብ የጎፍ የመንግስት ደን፤ በሰሜን የተሁለደሬ ወረዳና የደሴ ዙሪያ ወረዳዎች ያዋስኗታል። ከተማዋ ወደ ሪጆፖሊታን ከተማነት ካደገች በኋላ በአራት ክፍለ ከተሞች፤ በ14 የከተማ እና ስድስት የገጠር ቀበሌዎች ተዋቅራለች። የአየር ፀባይዋ በወይናደጋነት የሚመደብ ሲሆን፤ ይህም ከተማዋን ለኑሮ የተመቸ አድርጎታል። የከተማዋ ነዋሪ አማርኛን፣አፋርኛን፣ አርጎብኛን፣ ኦሮምኛ ቋንቋን አዋዶና አጣጥሞ የሚናገርባት የአብሮነትና የፍቅር ተምሳሌት የሆነ ህዝብ ነው። ይሄም ብዙ ባለሃብቶችን መሳብ ከሚችለው መልክዓ ምድሯ ጋር ተዳምሮ ከተማዋን የኢንቨስትመንት መዳረሻ በመሆን ተወዳጅነትን አትርፎላታል።

የኮምቦልቻ ሪጆፖሊታን ከተማ አስተዳደር በሀገራችን በተለየ ትኩረት ከሚመሩ የኢንዱስትሪ ከተሞች መካከል በግምባር ቀደምትነት የምጥጠቀስ ሲሆን፤ በአንጋፋው የኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ የስጋና የቆዳ እንዲሁም የቢራ ፋብሪካዎች በተጨማሪ በርካታ የመንግስታዊና የግል ፋብሪካዎችን በማካተት የኢንዱስትሪ ከተማነቷን አስመስክራለች።

ለኢንዱስትሪ ከተማነት ያስመረጣት ዋና ዋና ምክያች ደግሞ ለገቢና ወጭ ንግድ ምቹና ውጤታማ በመሆኗ ሲሆን፤ ለጅቡቲ ወደብ 440 ኪሎ ሜትር፣ ለአዲስ አበባ በ375 ኪሎ ሜትር፣ ለአሰብ ወደብ በ390 ኪሎ ሜትር፣ ለሰመራ ከተማ በ161 ኪሎ ሜትር ለክልሉ ዋና ከተማ ባህርዳር ደግሞ በ505 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ መገኘቷ ተመራጭ አድርጓታል።

በከተማዋ የሚገኙት የደረቅ ወደብ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ ደረጃውን የጠበቀ የኢንዱስትሪ ዞን፣ በከፊል የተጠናቀቀው የባቡር ሃዲድ፣ እንዲሁም የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ዋና መስመር መሆኗ ይበልጥ ተወዳጅና ተመራጭ ሆናለች። እ ስ ከ ቅርብ ጊዜ ባለው መረጃ መሰረት የኮምቦልቻ ሪጆ ፖሊታን ከተማ አስተዳደር ከ144 በላይ የሀገር ውሥጥና የውጭ ሀገር ባለሃብቶች መዋለ ንዋያቸዉን በማፍሰስ ከ180 በላይ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ገንብተውላታል። በኢንዱስትሪዎቿም ከ3000 በላይ ለሚሆኑ ነዋሪዎቿ የሥራ ዕድል ተፈጥረውላቸው ሕይወታቸውን ይመሩባታል።

እ.አ.አ. በ2017 ዓ.ም ጀምሮ በኮምቦልቻ ከተማ ኢንቨስትመንት እየተሳተፉ ከሚገኙ ድርጅቶች



አቶ ሐብታሙ ኃይሌ



አቶ መሀመድአሚን የሱፍ

መካከል የጣሊያኑ ኩባንያ ካርቪኮ ኢትዮጵያ አንዱ ሲሆን፤ አቶ ግርማ መታፈሪያ የድርጅቱ ፕሮዳክሽና ሜንተናንስ ማናጀር ናቸው። ፋብሪካው በዋናነት የስፖርት፣ የዋና እና ሌሎች ልብሶችን የሚያመርት ነው። በዓለም ላይ እንደ አዲዳስ እና ናይክ የመሳሰሉ ድርጅቶች ደግሞ የዚህን ኢንዱስትሪ ምርት የሚቀበሉ ደንበኞች ሲሆኑ በዓለም ላይ በጥራት ተወዳዳሪ ከሆኑትም መካከል የሚጠቀስ እንደሆነ ይናገራሉ።

ይህ ፋብሪካ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ይሰራ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የማስፋፊያ ቦታ በመውሰድ በሰፊው እየሰራ ነው። ኮምቦልቻ ለጅቡቲ ወደብ ያላት ቅርበት፣ የደረቅ ወደብ በከተማዋ አቅራቢያ መገኘቱ፣ የባቡር ትራንስፖርት መኖሩና ሌሎች መሰረተ ልማቶች መኖራቸው ብሎም ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል መኖሩ ድርጅቱ ኮምቦልቻን ሊመርጥ ችሏል።

ይህ ፋብሪካ በሰፊውና የረጅም ጊዜ እቅድን ይዞ ይሰራ የነበረ ቢሆንም፤ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት ከአንድ አመት በፊት ኮምቦልቻም የጦርነቱ ክልል ውስጥ ስለነበረች የድርጅቱ አመራሮችም ሆኑ ሠራተኞች ድርጅቱን ትተው መውጣቸውን ያስታውሳሉ። በዚህም ወቅት ትልልቅ ማሽኖች ውድመት ደርሶባቸዋል፤ ለስርቆትም ተዳርገዋል። አስር እቃ ጫኝና አውራጅ ማሽኖች መሰበራቸውንና እስከ 30 ቶን የሚያንቀሳቅሱ ማሽኖች ከጥቅም ውጭ ሆነዋል።

ይሁንና እነዚህ ሁሉ ውድመቶች ቢደርሱም ለባለሃብቶች መንግስት የሰጠው ትኩረት ከፍ ያለ በመሆኑና የድርጅቱ ባለቤትም በኢትዮጵያ ለሚያካሂዱት ኢንቨስትመንት ባላቸው ቁርጠኝነት በድጋሜ ወደ ሥራ ተመልሰዋል። ድርጅቱ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን 120 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ያረገ ሲሆን፤ በቀጣይም ይህንን የሚያጠናክር ይሆናል። ለ250 ዜጎችም የሥራ ዕድል ይፈጥራል። በአሁኑ ወቅት ከተማዋ መነቃቃት ላይ መሆኗን ይመሰክራሉ። በተለይም ከጦርነት ማግስት ላይ ሆና ከቀድሞ ሥራዋ ያናጠፋትን ትካዜ በመተው ወደ ተሻለ እንቅስቃሴ ለመግባት እየተውተረተረች ነው። ይሁንና አሁንም ቢሆን የግንባታ ግብዓቶችና የሲሚንቶ እጥረት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እጥረት፣ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በተፈለገው ልክ አለመገኘቱና የመሳሰሉት ችግሮች የኢንዱስትሪ ፈተና መሆናቸውን ይጠቁማሉ።

አቶ መስፍን አያሌው፣ አማር የግብርና ምርቶችን፣ የጨውና፣ ስኳር፣ ዱቄትና ሌሎችን ምርቶችን ለማሸግ የሚፈይድ ከረጢት ማምረቻ ፋብሪካ ዋና ሥራ አስኪጅ ሲሆኑ፤ ከተማዋ በጦርነቱ ወቅት የተፈጠረባትን ብዙ ችግሮችን አልፋ አሁንም ቢሆን ኢንቨስትመንትን እያፋጠነች መሆኑን ይናገራሉ። ባለፈው ዓመት ከተማዋ በጦርነት ቀጣና ውስጥ በነበረችበት ጊዜ ከፍተኛ ኪሳራ እንደደረሰ በማስታወስ፤ በወቅቱም ድርጅታቸው በዚህ ወቅት ከፉኛ ጉዳት እንደደረሰበት ይናገራሉ። ውድመት የደረሰባቸው ማሽኖች በብዛት ከውጭ ሀገር የሚገዙ ቢሆንም፤ የድርጅቱ ባለቤት ካላቸው ቁርጠኛ አቋምና ኢንቨስተመንት ፍላጎት የተነሳ በአጭር ጊዜ ማሽን ከውጭ በማስገባት ወደ ሥራ መመለሳቸው ይናገራሉ።

መንግስትም ለዘርፉ በሰጠው ትኩረትና እያደረገ ባለው ድጋፍ በአሁኑ ወቅት ሰራተኞችን ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመለሱ ጥሪ በማድረግ በሙሉ የማምረት አቅም ላይ መሆኑን ይናገራሉ። በአሁኑ ወቅትም የድርጅታቸው የሥራ አፈፃፀም 75 ከመቶ ሲሆን በሂደት ወደ መደበኛ ሥራው ሙሉ ለሙሉ የሚመለስ ይሆናል። ምርቶቻቸውንም በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ ከማድረግ በተጨማሪ ለውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብም እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል። ምንም እንኳን እነዚህ መነቃቃቶች ቢኖሩም አሁንም ቢሆን የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ ጉዳት ለደረሰባቸው ፋብሪካዎች የብድር አመላለስና የብድር እፎይታ ሥርዓት የዘርፉ ፈተናዎች በመሆናቸው መንግስት በልዩ ትኩረት እንዲመለከተው ጠይቀዋል።

የኮምቦልቻ ሪጂኦፖሊቲያን ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪና ኢንቨትመንት መምሪያ ኃላፊ አቶ ሐብታሙ ኃይሌ እንደሚሉት፤ ከተማዋ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ባለሃብቶችንና ኢንቨስትመንት የመሳብ ልምድ ያላት በመሆኑ በርካቶች ቀልባቸውን ጥለውባታል። በአሁኑ ወቅትም 53 ቢሊዮን ብር ኢንቨስትመንት እየተካሄደባት የምትገኝ ከተማ ናት። በዚህም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ሊደግፉ የሚችሉ ኢንቨስትመንቶችን እያስተናገደች ሲሆን፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችም የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

ለዓመታት ኢንቨስመንትን ስታሳልጥ የቆየችው ከተማ ግን ባለፈው ዓመት በነበረው ጦርነት ከፍተኛ ወድመት ደርሶባታል። በኢንዱስትሪዎች ላይ ትልቅ ዝርፊያ ተካሂዷል። ከኢንዱስትሪዎች በተጨማሪም አምራች ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በርካቶችም ከውጭ ሀገራት ያስመጧዋቸው ጥሬ ግብዓቶች ለዘረፋ፣ ውድመት እና ለብልሽት ተዳርገውባቸዋል።

ይሁን እንጂ አሁን ላይ ከተማዋ ከደረሰባት ወድመት ለማገገም ደፋ ቀና እያለች ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮችም ወደ ሥራቸው እየተመለሱ ነው። መንግስት ሠላም እና የሀገር ጥቅምን በማስቀደም ችግሮችን በድርድር ለመቋጨት መወሰኑም ከተማዋ ወደ ቀድሞ የኢንቨስትመንት ኮርደርነቷ ለመመለስ ምቹ እድል የሚፈጥር ነው።

እንደ አቶ ሐብታሙ ገለፃ፤ ምንም እንኳን ኢንቨስመንቱን የማነቃቃት ሥራዎች ከፌደራል ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር በትኩረት እየተሠራ ቢሆንም፤ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ ኢንዱስትሪን የሚያንቀሳቅስ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ የመሰረተ ልማቶች በሚፈለገው መጠን አለመሟለት ዛሬም ኢንቨስተሮች በተደጋጋሚ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች መሆናቸውን አልሸሸጉም።

የኮምቦልቻ ሪጂኦፖሊቲያን ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ መሀመድአሚን የሱፍ እንደሚሉት፤ ከተማዋ በርካታ ፀጋዎች ያሏት ሲሆን በርካቶችንም ለኢንቨስትመንት መሳብ የምትችል ናት። እንደ ከተማ አስተዳደር በተያዘው ጠንካራ የፖለቲካ አቋምና ባለሃብቶችን የማስተናገድ አቅም በርካቶች ትኩረታቸውን ከተማዋ ላይ አድርገዋል። ይህም በመሆኑ በየዓመቱ በርካታ ገንዘብ ፈሰስ እየተደረገባት የምትገኝ ከተማ ናት።

ኢንቨስትመንቱን የሚፈታተኑ በርካታ ጉዳዮች እንደነበሩ ያስታወሱት አቶ መሀመድአሚን፤ በአሁኑ ወቅት መፍትሄ እየተበጀላቸው መሆኑንም አብራርተዋል። ለአብነትም የመንገድ መብራት ጉዳይ ለነዋሪዎችም ሆነ ለኢንቨስተሮች አንዱ ጥያቄ ነበር። የመብራት መሰረተ ልማቶች በዋናነት በፌደራል መንግስት የሚሰሩ ቢሆኑም መንግስት ቀድሞ በከተማዋ ውስጥ የነበሩ ኃይል ተሸካሚ ምሰሶዎች ሙሉ ለሙሉ በአዲስ ምሰሶዎች እንዲቀየሩ አድርጓል። ይህም ችግር በመፈታቱ የመብራት ችግርም እየተፈታ ሲሆን፤ እነዚህ ችግሮች ሲስተካከሉ ኢንቨስትመንቱን ያሳድገዋል።

ከተማዋ በ2000 ዓ.ም የመንገድ መብራት ተሰርቶላት ነበር። ይሁንና ግን የተሰራበት መንገድ የጥራት ችግር ስለነበረበት እስከዛሬም ድረስ ባለመስራቱ ጉዳዩ አከራካሪ ሆኖ ቆይቷል። ፍርድ ቤት ድረስ ሄዶም በኮንትራክተሩ እና በክልሉ የህግ ክፍል መካከል ክርክርም ሲካሄድ ቢቆይም፤ ችግሩ ለብዙ ዓመታ ሊፈታ አልቻለም። ከጥራት ጋር ተያይዞ ያለው ችግርም ሊፈታ አልቻለም። በመሆኑም የከተማ አስተዳደሩ በአዲስ መንገድ በ79 ሚሊዮን ብር በመበጀት በአዲስ መንገድ እየሠራው ነው። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም መንገዶቻችን ጨለማ ስለሆኑ ወንጀሎች ተበራክተው ነበር። ሕብረተሰቡ በዚህ የተነሳ ቅሬታ ያቀርብ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን የነዋሪዎችን ሆነ የባለሃብቶችን ቅሬታ ለማቃለል የተወሰደ አፋጣኝ መፍትሄ መሆኑንም ነው አቶ መሀመድአሚን ያብራሩት።

ከዚህም በተጨማሪ ከተማዋ ጦርነትው ካደረሰበት ጫና ወጥታ ወደ ቀድሞ እንቅስቃሴዋ እየተመለሰች መሆኗ ትልቅ ተስፋ ነው። በጦርነቱ ወቅት ገንዘብ ስናወጣ የነበረው ለሀገር መከላከያ ሰራዊትና ለጥምር ጦሩ ደጀን ለመሆን ነበር። ጦርነት ባለበት አካባቢ ኢንቨስትመንት አይመጣም። የትግራይ ህዝብና የወሎ ህዝብም በመልክዓምድርና በአኗኗሩም የሚቀራረብና የሚዋሰን ነው።

በመሆኑም የወሎና የትግራይ ህዝብ ተመልሶ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሕይወቱ እንዲተሳሰር እየሰራን ነው፤ ወደ ቀድሞ መስተጋብራቸው እንዲመለሱም እንፈልጋለን። እኔም እንደ ዜጋ ለዚህ ሠላም የሚከፈለውን ሁሉ መስዕዋት ለመከፍል ዝግጁ ነኝ። ስለዚህ ሠላሙ ማህበራዊ፣ ፖለቲከዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው በመሆኑ በትኩረት ልንሠራበት ይገባል። በጦርነቱ ሳቢያ ጉዳትና ዝርፊያ ደርሶባቸው የነበሩ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ፣ በማገዝ እና በመከታታል ወደ ሥራ እየተመለሱ ሲሆን፤ የውጭ ኢንቨስተሮችም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ሥራቸውን እየጀመሩ መሆኑን አቶ መሐመድአሚን አረጋግጠዋል።

# ጎሜ

# ሳያነቡ የሚጽፉ

ግርማ መንግሥቴ

ሰሞኑን አብርሆት ቤተ-መጻሕፍት ባረፈበት ክልል ውስጥ አንድ ሁነት ተካሂዶ የነበረ ሲሆን፣ እሱም "ንባብ ለምክንያታዊነት" በሚል መሪ ቃል የተከናወነው የንባብ ሳምንት መርሀ-ግብር ነው። በቃ፣ ይኸው ነው። ይኸው ይሁን እንጂ ሁለት ጥልቅ እሳቤዎች ("ንባብ" እና "ምክንያታዊነት")ን ይዟልና ለዛሬ ልንነጋገርበት ወደድን።

ማንበብ ለማንም ብርቅ አይደለም፤ በየትኛውም ዘመን ብርቅ ሆኖ አያውቅም። በተለይ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የመብላትና መጠጣትን ያህል የእለት ተ'ለት ተግባር ነበር (ውይ ... ውይ ...፣ "ነበር" ማለት እንዴት ያስጠላል?)። ይህንን ስንል ደግሞ (ስለ ምክንያታዊነት ነውና የምናወራው) ያለምክንያት አይደለም።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪካችንን ስንመረምር የምንደርስበት እውነት ቢኖር፣ "የፍቅር እስከ መቃብር ደራሲ ማን ነው?" ተብላ የተጠየቀችው የ11ኛ ክፍል ተማሪ "ኃይሌ ገብረሥላሴ" ብላ እንደ መለሰችው ሳይሆን፣ አንባቢ ትውልድ የነበረበት ዘመን የነበረ መሆኑን ማሳየት ነው። ለዚህ ደግሞ መረጃና ማስረጃው ኢትዮጵያ የፈላስፎች ምድር የነበረች መሆኗ ነው። (ኤጭ፣ ይሄ "ነበር" አሁንም በ"ነበረች" ተሸፍኖ መጣ።)

The African Enlightenment (Dag Herbjørnsrud፣ ዲሴምበር 2017) በሚል ርእስ ለንባብ የበቃው ጥናታዊ ጽሑፍ እንደሚያስረዳው ከአለማችን ስመ ጥር ፈላስፎች (ጆን ሎክ፣ ሁም፣ እና ካንት) ሁሉ በፊት እነሱ ደረሱበት የተባሉትን አዳዲስ ሀሳቦች ከክፍለ ዘመናት በፊት ኢትዮጵያዊያን በዋሻ ውስጥ ተግብረውት የተገኘ መሆኑን ለማመን በሚያስቸግር አገላለፅ The highest ideals of Locke, Hume and Kant were first proposed more than a century earlier by an Ethiopian in a cave. በማለት አስፍረውት መገኘቱ ከመረጃም በላይ፣ ከማስረጃ ከፍ ያለ ነው። ይህ ደግሞ በበኩሉ የኢትዮጵያን የአንድ ዘመን ከፍታ ያሳያልና ጥናቱን ስናደንቅ በኩራት ነው።

እኝሁ የGlobal Knowledge: Renaissance for a New Enlightenment (2016) ደራሲ በቀዳሚ ማስረጃነት ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብን የሚጠቅሱ ሲሆን በሰለጠነው አለም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ዲሞክራሲና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቅ ማለት መነሻው (ምክንያቱ ማለት ነው) ይኸው የኢትዮጵያ ፍልስፍና መሆኑን እየጠቀሱና እያጣቀሱ ይገልፃሉ። ታዲያስ ውድ አንባቢ፣ በኢትዮጵያ አንባቢ ትውልድ አልነበረም ይላሉ?

ዛሬ ዛሬ በአገራችን የሚታየው ያው ስብሀት ገብረእግዚአብሄር በአንድ ወቅት ብሎት እንደነበረው የተገላቢጦሽ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። "ምክንያት?" ሲባሉ "ደሞ ለምክንያት ..." ይሉና ምክንያታቸውን ይደረድሩታል።

እንዲህም እያሉ፡-

ዛሬ የዩኒቨርሲቲዎቻችን ቁጥር፣ በስንት እጥፍ እንደሆነ እንኳን ለማስላት በሚያስቸግር ሁኔታ አድጓል። የምሩቃኖቻቸውን ቁጥር ከጨመርን ከሰማይ ኮኮብ ከምድር አሸዋ አይተናነሱም ነው የሚባለው። የዶክተርና ፕሮፌሰሮቹ እንኳን ብቻውን ቢወሰድ ከድሮ አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ከሚያስመርቋቸው (በስንት እጥፍ እንደሆነ ተረሳ እንጂ) ይበልጣል ይላሉ። ይህ ሁሉ ባለበት ሁኔታ አንድ የሚያዝናና ነገር ቢኖር የጥናትና ምርምር ስራዎች ከድሮው ጋር ሲወዳደሩ የድሮዎቹ ከዘንድሮዎቹ (በስንትና ስንት እጥፍ እንደ ሆነ ተረሳ እንጂ) የሚበልጡ መሆኑ ነው። የሚያዝናናውና የሚያሳዝነውም ይኸው ነው። ከሁሉም ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ "እኔ መጽሐፍ አላነብም።" የሚል ባለ ዲግሪ በአደባባይ ሲንጎማለል ማየቱና ቀረርቶውን መስማቱ ነውና ድሮና ዘንድሮን እዚህ ማወዳደር አንድ ራሱን የቻለ ልግጫ በመሆኑ በምድርም በሰማይም ያስጠይቃል የሚሉ መኖራቸው ደግሞ ሌላውና ኮስተር ያለው አስተያየት ነው።

ይህ ብቻም አይደለም፣ እነዚህ "ተቺዎች" (ከፈለግን "የድሮ ናፋቂዎች"ም ልንላቸው እንችላለን) የማይሉት የለም፤ አንስተው የማያፈርጡት ጉድ አይገኝም፤ ሲያስፈልጋቸው "የፌስቡክ መንጋ ..." በማለት ይጀምሩና "ሰውዬ አታናግረኝ ..." በማለት ፈንጠር ፈንጠር እያሉ፣

> **"ከእውቀት ነፃ" እንደሚባለው ሁሉ፣"ከወረቀት ነፃ ..." የሚል ወፍ ዘራሽ አነጋገር በአገራችን፣ በተለይም በከተሞች፤ በተለይ በተለይ በተቋማት ሳይቀር ከች ብሏል**

እያናገራቸው ያለውን ሰው ባለበት ገትረው ፈትለክ ይላሉ።

አንድ "'ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል' በሚለው ይስማማሉ?" በማለት ጥያቄ ያቀረብኩላቸው ሰውዬ የተናገሩትን እዚህ ማንሳት ቢያስፈራም ስለማያስበረግግ እንጥቀሰውና እንለፍ።

ጋሼ "'ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል' በሚለው ይስማማሉ?"

ኤዲያ፣ ሙሉ አደረገ ጎደሎ ምን ዋጋ አለው። ይህ እሚባለው እኮ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያነብ ሲኖር ነው፤ አይደለም እንዴ? (መልሱን ለአንባቢ ትተን እንለፍ።)

በዚህ በያዝነው በ21ኛ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ "አንባቢን የበላ ጅብ አልጮህ ብሏል" የሚለውን አገላለፅ መስማት አዲስ ነገር አይደለም። እንግዳ ጉዳይም ሆኖ አያውቅም። በቃ፣ አንባቢን የበላ ጅብ አለ። ግን "እኔ ነኝ ..." ብሎ ሲጮህ አይሰማም። ብቻ ተሰማም አልተሰማም አንባቢ እንደ ሆነ ተበልቷል (ሲያስፈልግ በቴክኖሎጂ፣ አልያም በሱስ ... ማለት ይቻላል፤ ብቻ አንባቢ ተበልቷል።)። ታዲያ ባይበላ ኖሮ የት ገባ? ምክንያታዊነትስ ከነ ልጅ ልጆቹ እምጥ ይግባ ስምጥ አይታወቅም ነበር? ይታወቅ ነበር።

የሰይጣን ጆሮ አይስማውና፣ አንዳንዶች እንደሚሉት በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ወቅት ማጣቀሻ መጻሕፍትን የሚጠቁሙት ከመምህሩ ይልቅ አንዳንድ ተማሪዎች ናቸው። የበለጠ አንዳንዶቹ እንደሚሉት ደግሞ መምህሩ ከተማሪው በንባብ የሚቀድመው በአንድ አንቀፅ ብቻ ነው። ለዚህ ነው የትምህርቱ ጥራት ሰማየ ሰማያት የደረሰው ..... ነው የሚሉት። ጆሮ አይሰማው የለምና ... ነገሩ ብዙ ነው።

ሌላውና በሹክሹክታ ሲወጋ (ወግ) የሚሰማው በአገራችን፣ በተለይም በዚሁ ባለፈው ሳምንት "ንባብ ለምክንያታዊነት።" በሚል መሪ ቃል የንባብ ሳምንት በተከበረባት መዲናችን፣ እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ሳይቀር (እንደውም ይብሳል ነው የሚባለው) ሳያነቡ የምጽፉ ቁጥራቸው እየተበራከተ የመምጣቱና ከየእውቀት ምንጭነት ይልቅ አደንቋሪነታቸው ሚዛን እየደፋ የመምጣቱ ጉዳይ ነው።

ነፍሱን ይማረውና ደምሴ ፅጌ በአንድ ወቅት እንደዚህ አይነቶቹ ("ከእውቀት ነፃ"ዎቹ) እየበዙ መምጣታቸውና ከስራዎቻቸው ምንም አይነት ረብ በማጣቱ ምክንያት "... ምን እነዚህ፣ ወይ አያነቡ፤ ወይ አይጠይቁ ..." በማለት ምሬቱን መግለፁን አንብበናል። በአንባቢነቱና ደራሲነቱ የተከበረ ስፍራን የያዘው ስብሀትም፣ እያባበለም ቢሆን፣ ወጣቱን ("እሳቱ ትውልድ ...፣ "ነቄው ትውልድ ..." በማለት) "አንብቡ" ሲል መሸንቆጡ አልቀረም። "ካላነበብክ ታዲያ ምን ልትሆን ነው ...?"

በዓሉ ግርማም አፍቃሬ አንባቢ ሲሆን፣ "ከአድር ባይ ብዕር ባዶ ወረቀት ይሻላል።" የምትለው ዘመን ተሻጋሪ አባባሉም እየተነጋገርንበት ያለውን፣ ምክንያታዊነትን የሚያፀና ነው እዚህ ሊጠቀስ የግድ ይሆናል።

በተለይ ሳት ብሏቸው ወደ ማህበራዊ ሚዲያው ጎራ ያሉ (የድሮ ናፋቂ) ጎምቱዎች በምሬት ሲናገሩ እንደሚሰማው ከሆነ የድሮዋ ኢትዮጵያ የለችም። ድሮ ድሮ መሳደብ ነውር ነበር ነው የሚሉት። ብልግና ቃላትን አይደለም መጠቀም፣ ማሰብ እንኳን የሚታሰብ አይደለም። ባጭሩ፣ ወዴት እንደ ሆነ አይታወቅም እንጂ፣ ምክንያታዊነት ከኢትዮጵያ ውስጥ ጓዙን ጠቅልሎ ከሄደ፤ በመንጋነት ከተተካ ሰንብቷል። አንባቢነት አይደለም በአግባቡ ማዳመጥና መደማመጥ እንኳን ተረት እየሆነ ነው። መጯጯህና አለመግባባት ቦታውን ከያዙት ጊዜው ዛሬ ሳይሆን ቆየ።

ማንበብ ስንትና ስንት ሳይንቲስቶችን እንዳላፈራ፣ ስንትና ስንት ከአለም ቁጥር 1 ባለ ሀብቶችን እንዳላበረከተ፣ ስንትና ስንት ወታደራዊ ጠበብትን ለአለማችን እንዳላስገኘ፤ ስንትና ስንት ፈላስፎችን "እነሆ በረከት ..." እንዳላለ ሁሉ ዛሬ አይንህ ላፈር ተብሎ "እኔ መጻሕፍት አላነብም" እሚባልበት ዘመናዊ ዘመንና ትውልድ ላይ ተደረሰና ታረፈው።

ይህ ጸሐፊ "መጻሕፍት ትፈልጋለህ? አራት ሺህ መጻሕፍት አሉኝ። ልሰጥህ እችላለሁ።" ያለው ሰው አጋጥሞት የነበረ ሲሆን፣ "በምን በምን ጉዳይ ላይ የተጻፉ ናቸው?" ሲል ላቀረበው ጥያቄ "አይ፣ አላነበብኳቸውም። ፒዲኤፍ ናቸው።" የሚል ምላሽን እንዳገኘ መቸም የሚረሳው ጉዳይ አይደለም። (እዚህ ላይ ይሄም አለ ለማለት ነው እንጂ በፒዲኤፍ ያሉ መጻሕፍትን ለማጣጣል አይደለም።)

"ከእውቀት ነፃ" እንደሚባለው ሁሉ፣"ከወረቀት ነፃ ..." የሚል ወፍ ዘራሽ አነጋገር በአገራችን፣ በተለይም በከተሞች፤ በተለይ በተለይ በተቋማት ሳይቀር ከች ብሏል። (ወረቀት እየሸጡ፣ መተዳደሪያቸውም እሱው በሆኑት ሳይቀር) መቀንቀኑና መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን ንባብ ጠል ትውልድ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ መሆናቸው ነው። ይህ ከየት የተገኘ "ቁም ነገር" እንደ ሆነ ባይታወቅም (ለምሳሌ አሜሪካን አገር በአመት ከ500ሺህ በላይ መጻሕፍት (ጋዜጦችና መጽሔቶችን፣ ማስተማሪያና አጋዥ ስራዎችን ሳይጨምር) ይታተማሉ)፣ የአቀንቃኞቹ ፍላጎት በቴክኖሎጂ አመጣሽ መሳሪያዎች መጠቀምን (መላላክን) መስበክ ይመስላል። ያ ከሆነ ቋንቋው ይህ አይደለምና፤ አገላለፁ የተወላገደ ነውና በአስቸኳይ መታረም አለበት ስንል አሁንም በትህትና ነው።

በአመታዊው "የንባብ ሳምንት" መርሀ-ግብር መሪ ቃልን መሰረት ያደረገው ርእስና ርእሰ ጉዳያችን እንደሚነግረን ከሆነ ንባብና ምክንያታዊነት የሚነጣጠሉ አይደሉም፤ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው ማለት ነው። በመሆኑም፣ "ማንበብ" ከሌለ "ምክንያታዊነት" የለም ማለት ነው። ለምክንያታዊነት ደግሞ ማንበብ የግድ ነው ማለት ነው - እንደምናውቀውም፣ እንደ መሪ ቃሉም።

ከመሪ ቃሉ መረዳት እንደሚቻለው ያለ ንባብ ምክንያታዊነት የለም። ምክንያታዊነት ከሌለ ደግሞ፣ ከላይ የጠቀስናቸው "የድሮ ናፋቂ" ጎምቱዎች እንደ'ሚሉት "መንጋነት ..." ይሰፍናል ማለት ነው። አሁንም፣ እንዚሁ ሰዎች ሲናገሩ እንደሚደመጠው ደግሞ፣ "መንጋነት ... ሰፈነ" ማለት ደግሞ ሰብአዊነት ነጥፎ እንስሳዊነት በስፍራው ተተካ ማለት ነውና ጉዳዩ ያወያያል፤ ያነጋግራል፤ ያመራምራልም።

እዚህ ላይ አንድ አቢይ ጉዳይ እናንሳ። ልብ በሉ፣ የንባብ ሳምንቱ መርሀ-ግብር የተካሄደው ከአዲሱና ዘመናዊው አብርኆት ቤተ-መጻሕፍት ጋር በተያያ ስፍራ (አራት ኪሎ) ላይ ነው። "አብርኆት" ማለት ደግሞ በአቻ ስያሜው Enlightenment ነው። Enlightenment ማለት ደግሞ በርካታ የአለም አገራት ከነበሩበት አዘቅት የወጡበት የሽግግር ዘመን እና ራሱን የቻለ የፍልስፍና አካል ሲሆን፣ ማእከላዊ ትርጉሙም (ሰዎች ምክንያታዊነታቸውን በይፋ የሚያሳውቁበት፣ ምክንያታዊ የሚሆኑበት፣ ሰዎች ሁለንታን ጠንቅቀው የሚያውቁበት፣ እና የአኗኗር ዘይቤያቸውን የሚያሻሽሉበት (The use and celebration of reason, the power by which humans understand the universe and improve their own condition.) ሁኔታ ማለት መሆኑን ልብ ማለት ያሻል። ይህ በበኩሉ የሚያሳየን አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ቢኖር ማንበብ ከምክንያታዊነት ጋር ብቻ ሳይሆን ከአብርኆት ጋር ሁሉ የጠበቀ ግንኙነት፣ ትስስር ... ያለው መሆኑን ነው። ለዚህ ማሳያው ደግሞ በአብርሆት ላይ ጥርሳቸውን የነቀሉ ምሁራን፣ ከላይኛው በማስከተል "የሰው ልጅ ምክንያታዊነት ዋና አላማ ማሳያ ተደርገው የሚወሰወዱት ደግሞ እውቀት፣ ነፃነት፣ እንዲሁም ደስታ" መሆናቸውን፣ "The goals of rational humanity were considered to be knowledge, freedom, and happiness." ማለታቸው ነው። ባለ ዲግሪዎቹ፣ እነ "እኔ መጽሐፍ አላነብም"፣ እነ "ንባንብ ለምኔ ..." እንዳይሰሙን ብለን ነው እንጂ ብዙ ማለት በተቻለ ነበር።

ከእነ ባለ ዲግሪዎቹም ሆነ "ከእውቀት ነፃ"ዎቹ፣ ከእነ "እኔ መጽሐፍ አላነብም" ... ባይ ጎምላሌዎቹ በተቃራኒ ያሉቱ ሲሉ እንደሚሰማው ከሆነ (ለምንድን ነው ግን ጋዜጠኞች ይህችን "... ከሆነ ..."ን በፍቅር የሚወዷት? "... እንደ ተናገሩት ከሆነ"፣ "... እንዳሉት ከሆነ..."፣ "እንደሚሉት ከሆነ ...") "የማያነብ ሰው እና ደም የሌለው ሰው አንድ ነው።" (አናብራራውም።)

ማንበብ ከእነ ተጣማሪው "ማንበብና መጻፍ / ዋናው ቁም ነገር ..." ተብሎ ተዘፍኖለታል። "አንብቡ / እናንብብ ..." ተብሎም ተዜሞለታል። አያሌ መጻሕፍት ስለ ንባብና ጥቅሙ ለህትመት ብርሀን በቅተዋል። የእምነት ተቋማት ያለ ንባብ ግንዛቤ እንደ ሌለ አስተምረዋል፤ እያስተማሩም ነው። ያለ ግንዛቤ ደግሞ እምነት ከንቱ ነው።

የማንበብንም ሆነ ምክንያታዊነትን የተመለከቱ የጥናትና ምርምር ስራዎች እለት በእለት ሲበረከቱ ዘመናትን አስቆጥረዋል። ምሁራን የሚያነብን ሲያወድሱ፤ ፀረ-ንባብ እንቅስቃሴን ሲያወግዙና እነ "ንባብ ጠሌ"ን ሲነቅፉ እድሜያቸውን ፈጅተዋል።

በልቶ ለሚከሳ፣<br>
ተመክሮ ለሚረሳ፤<br>
ለዚህ ምክር፣<br>
ለዚህም ምግብ ንሳ።

እንደ ተባለው ምክራቸውን የሰሙ ሲለወጡበት ተመክረው የረሱትም (አብነት አጎናፍር "ሲመክሩህ ውለው ሳትሰማ ግባ ..." እንዳለው) ወደ "... መንጋነት" (ከላይ የጠቀስናቸው "የድሮ ናፋቂዎች" እንደሚሉት ማለታችን ነው) እያቀኑ ይገኛሉ። (በነገራችን ላይ፣ መንጋነት ከጎዳቸው ማህበራዊ ሚዲያዎች አንዱ ፌስቡክ ሲሆን፣ ኤፍቢ ቀድሞ የነበሩት ምሁራን ታዳሚዎቹ ወደ ቲውተርና ቴሌግራም እንዲጎርፉ ያደረጋቸው ይሄው መንጋነት መሆኑን ልብ ይሏል።)

ድሮ በሚያነብ የሚቀናበት ዘመን ሲሆን፣ ዘንድሮ የማያነብ የሚሞገስበት ዘመን ነው። ዘንድሮ፣ "ሳያዩ የሚያምኑ ...." በሚለው ተሸውደውም ይሁን ሌላ ለጊዜው ባይታወቅም፣ ሳያነቡ የሚጽፉ በርካቶች የሆኑበት፤ ድሮ ሳያነቡ የማይጽፉ የሞሉበት ዘመን ነበር። ድሮ መጽሐፍ በእጅ መያዝ (ይዞ መታየት) የሚያስመሰግንበትና የምሁርነት፣ አንባቢነት ምልክት የነበረበት ዘመን ሲሆን፤ ዘንድሮ ማዳመጫን አንጠልጥሎ፣ መስሚያንም በእሱው ደፍኖ ክው ክው ማለት፤ ከራስ በራስ መጠፋፋት፣ ድምፃዊ ዘሪቱ ከበደ "ቴክኖሎጂ በላይ በላይ / ሰው ከራሱ እንዳይተያይ ..." እንዳለችው የሆነበት ዘመን ነው።

ምንም እንኳን "ዘመን የራሱን ሰው (ትውልድ) ይፈጥራል" ቢባልም፣ የእነ ሎሬት ፀጋዬ፣ ሀዲስ አለማየሁ ዘመን እነሱን እንደ ፈጠረው ሁሉ፣ የአሁኑ ዘመንም እነ አዳም ረታን፣ ቴዲ አፍረሮን ... እንደ ፈጠረ ለማሳየት እንጂ "ጫማው ልክ" የሆነ ትውልድ በነበረበት አገር "ጫማው ሰፋፊ ..."፤ "... ጎመን ቀራፊ" ትውልድ ይፈጠራል ማለት አይደለም። በመሆኑም፣ ፈላስፋ በነበረበት አገር የበለጠ ፈላስፋ፤ አንባቢ በነበራት አገር የተሻለ አንባቢ ... ይፈጠራል እንጂ ሎሬቱ እንዳለው ሁሉ ነገር "... ምድረ በዳ" ይሆናል ማለት ሊሆን አይገባውምና፣ ምክንያታዊነት የግድ ያስፈልጋልና፣ ምክንያታዊ መሆን ከሰብአዊ ባህርያት አንዱ ነውና እናንብብ፤ ሳያነቡ የሚጽፉ ከመባል ይሰውረን !!!

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# የገና ጨዋታ ባህላዊና ጥበባዊ ትውፊቶች

ዋለልኝ አየለ



ተፈጥሮን መሰረት ባደረገው በኢትዮጵያ የወቅቶች ምድባ አሁን የበጋ ወቅት ነው። በበጋ ወቅት በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል የእረፍት ወቅት ነው። በእንዲህ አይነቱ የእረፍት ወቅት ደግሞ ገና፣ ጥምቀት፣ ሰርግና ሌሎች ጉዳዮች ይበዛሉ። እነዚህ ወቅቶች የጨዋታና የደስታ ናቸው።

ወጣቶችና ልጃ ገረዶች የደስታ ጊዜያቸው ነው። አዋቂዎችም ቢሆን ከሌሎች ወቅቶች በተለየ የሚጫወቱት በዚህ በበጋ ወቅት ነው። በበልግ እና በክረምት ወራት ሰርግ ወይም ሌላ ጉዳይ ቢኖር እንኳን ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት ዘና የሚባልበት አይደለም። ቢያንጎራጉሩም በሥራ ቦታ ላይ ሆነው ነው። በዚህ በገና ሰሞን የበጋ ወቅት ግን ጎረቤት ከጎረቤት እየተጠራሩ ቤት ውስጥ ነው።

ለልጆች ግን የተለየ ቦታ አለው። ‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ፤ በገና ጨዋታ የለም ሎሌ ጌታ›› የተባለውም ለልጆች ነው። የገና ወቅት የበጋ ወቅት ነው። በዚህ ወቅት ልጆች የሥራ ጫና የለባቸውም። የግብርና ሥራ አይታዘዙም፤ ከብትም አይጠብቁም። በዚህ ወቅት ሰብል ስለሚሰበሰብ ከብቶች አይጠበቁም። ስለዚህ ልጆቹ ገና ሲጫወቱ ቤተሰብ ተቆጣኝ አልተቆጣኝ ብለው ሳይሆን በሙሉ ነፃነት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ለአሸንዳ ለልጃ ገረዶች እንደሚሰጠው ነፃነት በገና ጨዋታም ለልጆች ነፃነት ይሰጣል።

በነገራችን ላይ የገና ጨዋታ በበጋ ወቅት መሆኑ ወሩን ሙሉ ነፃነት ስለሚሰጣቸው እንጂ ለበዓሉ ዕለት ብቻ ከሆነ በክረምት ወራት ራሱ ይሰጣል። ለምሳሌ ለፍልሰታ (ነሐሴ 16) እና ለእንቁጣጣሽ ልጆች እንዲጫወቱ ተብሎ ለእዚያን ቀን አባቶች ናቸው ከብት የሚጠብቁት። አባቶች እንኳን ባይመቻቸው ሌላ በጎልማሳነት ዕድሜ ላይ ያለ (ጨዋታውን የማይሄድ) ሰው ከብት ይጠብቃል እንጂ ለዚያን ዕለት ልጆች ለጨዋታ ነፃነት ይሰጣቸዋል።

ወደ ገናችን እንመለስ። የገና ጨዋታ ብዙ የተባለለት ነው። አሁን ላይ ከገጠር ይልቅ ወደ ከተማ ያዘነበለም ይመስላል (በእርግጥ ብዙ ባህሎች ከገጠር ይልቅ ወደ ከተማ እየገቡ ነው)። የገና ጨዋታ ከባህል ስፖርቶች አንዱ ሆኖም እውቅና ተሰጥቶታል። የገና ጨዋታ ራሱን ችሎ የመገናኛ ብዙኃን የዜና ሽፋን ለመሆን በቅቷል። ጨዋታውም የራሱ የሆነ ህግና ደንብ ያለው ነው። የራሱ የሆነ ጥበብ አለው።

ሌላው የገና ጨዋታ ጥበብ አዳጊዎች (ልጆች) ሲጫወቱ እርስበርስ የሚለዋወጡት የቃል ግጥም ነው። ይወዳደሳሉ ይተራረባሉ። በተለይም በጨዋታው የተሸነፈው ቡድን በአሸናፊዎች ይተረብበታል፤ አሸናፊዎች ደግሞ የድል መልዕክት ባላቸው ስንኞች ይጫወታሉ። መጭውን የገና በዓል ምክንያት በማድረግ ስለገና ጨዋታ አንዳንድ እንበል።

የገና ጨዋታ ሁለት ቡድኖች ጎራ ለይተው የሚጋጠሙበት ልዩ ባህላዊ ትዕይንት ነው። ለሁለቱ ቡድኖች እኩል እኩል ቁጥር ያላቸው ተጋጣሚዎች ላይኖራቸው ይችላል። ያንደኛው ቡድን በርከት ብሎ፣ የሌላኛው ቡድን አነስ ያሉ ተጋጣሚዎች ሊይዝ ይችላል።

አንደኛው ቡድን ከቀኝ ወደ ግራ ከያዘ፣ ሌላኛው ቡድን ደግሞ ከግራ ወደ ቀኝ ያለውን ስፍራ ይይዛል። አቅጣጫውን ያልለየ ተጫዋች ካለ፣ ‹‹ሚናህን ለይ›› ተብሎ፣ ካስፈለገም በዱላ ቺብ ተደርጎ፣ ቦታውን ይይዛል። በጨዋታ መሃል ሚናውን ስቶ በሌሎች ሚና በኩል ከተገኘ ‹‹ከሚናህ!›› የሚል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። በሰሜኑ በተለይም በአማራ አካባቢዎች ‹‹ጥንጓን›› ወይም ‹‹ሩሯን›› የመቱበት የዱላው ራስ ‹‹ገና›› ይባላል። ከወደ ራሱ እንደ ከዘራ ቆልመም ያለ ዱላ ነው።

የገና ጨዋታ አሁን በዘመናዊ መልኩ በከተሞች ከምናየው ይለያል። በስፖርታዊ ውድድር ውስጥ በገባው ዘመናዊ የገና ጨዋታ ህግ መሰረት፣ ዱላውን (ገናውን) ወደ ላይ ማንሳት አይቻልም። በጥንታዊው ወይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በሚደረገው የገና ጨዋታ ላይ ግን እንደተፈለገው በማንሳት፣ ሩሯን (ጥንጓን) አክርሮ መለጋት ይቻላል።

ሌላው ደግሞ በዘመናዊው የገና ጨዋታ ስፖርት፣ ሩሯ የምትገባበት (የምትለማበት) ሥፍራ እንደ እግር ኳስ የግብ ሥፍራ ያለው ነው። በጥንታዊው ጨዋታ ግን የገና ጨዋታው የሚካሄድበት ሜዳ ወይም የእርሻ ማሣ፣ ሁለቱም ጫፎች የግብ ወይም የመልሚያ ቦታዎች ናቸው። ከሜዳው ወይም ከማሳው ስፋት የተነሳም ተጫዋቾቹ እንደ ልባቸው እየሮጡ ይጫወታሉ። ጨዋታው በውጤት አሊያም በሽንፈት እየታጀበ ይቀጥላል።

አንዱ ቡድን ሩሯን (ጥንጓን) እንዳለማ ወይም እንዳገባ በተቃራኒው ቡድን ላይ የተረብ መዓት ይዥጎደጎዳል። በገና ጨዋታ ላይ የሚሰነዘሩ ተረቦች ታዲያ እንደ መዝናኛና እንደ ማድመቂያ ነው የሚቆጠሩት። የሚተርበው ቡድን እንኳን በተረቡ ይዝናናል ይስቃል እንጂ ቂም መያዝ ብሎ ነገር በገና ጨዋታ አይታሰብም። ተሸናፊውም በእልህ ለማሸነፍ ይነሳሳል እንጂ በጨዋታ አድማቂው ተረብ አይቆጣም።

በጨዋታው ላይ የሚሰነዘሩ ወይም የሚወረወሩ ተረቦች በአብዛኛው በአካባቢ ገፅታ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ለምሳሌ ቁመት፣ እርዝመትና እጥረት፣ ውፍረትና ቅጥነት ወዘተ...

‹‹አሲና በል አሲና ጋማዬ

እያሃ ... አሲና ጋማዬ››... እያሉ ተጋጣሚዎች ጨዋታውን ያደሩታል።

ለምሳሌ አጫጭሮቹን የቡድን አባላት ለመተረብ አሸናፊዎቹ እንዲህ ይላሉ።

ይህን ወዳጅ ብላ ታስከትለዋለች
አንድ ቀን ጩልሌ ታስወስደዋለች

አጭሮቹ በተራቸው ደግሞ፡-

ረጅም ነህና ሞኝነት አታጣም
እቆርጥልሃለሁ አሳጥሬ በጣም
ይኸን ረጅሙን ጎምዶ ጎማምዶ
ግማሹን በርጩማ ግማሹን ማገዶ

እያሉ የአፀፋ ምላሹን ያዥጎደጉዱታል። አሁንም ወፍራሞች ደግሞ ቀጭኖችን እንዲህ ይሏቸዋል፤

ሲሄድ ቅትር ቅትር ሲበላ እንዳንበጣ
ወዘና የሌለው የጨጓራ ቋንጣ

የተረብ በትር ያረፈባቸው ቀጭኖችም ከአፀፋ ምላሽ አይቦዝኑም፤

እየው አካሄዱን አረማመዱን
እንደ ቃሪያ ሎሚ ወጥሮ ሆዱን

በጥንቱ የገና ጨዋታና አሁንም በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ሴቶች ባይጫወቱም በሜዳው ዙሪያ ሆነው የሚደግፉትን ቡድን ያበረታታሉ፤ የሚነቅፉትን ደግሞ በተረብ ይሸነቁጡታል።

ወንድ ነው ብዬ ብሰጠው ጋሻ
ለእናቱ ሰጣት ለአመድ ማፈሻ
ወንድ ነው ብዬ ብሰጠው ጦር
ለአባቱ ሰጠው ለቤት ማገር

እያሉ የገናን ጨዋታ ያደምቁታል።

ገና ጨዋታ በትክክል በአገራችን መቼ እንደተጀመረ በጽሁፍ የተደገፈ መረጃ ባይገኝለትም ከክርስቶስ ልደት በፊት ይዘወተር እንደነበር ይነገርለታል። በዚህም የክርስቶስ ልደት (ገና) ይከበራል። እረኞች የገና ጨዋታን ከታህሳስ ጀምሮ እስከ ጥር እና ከዚያም እስከ ክረምቱ መግቢያ ድረስ ይጫወቱት እንደነበር አባቶች ይናገራሉ። በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የገና ባህላዊ ስፖርት በስፋት ይተገበር እንደነበርም ይነገራል።

በገና ጨዋታ ልጆች ልክ እንደ ሆያ ሆየ በየቤቱ እየዞሩም ይጫወታሉ።

በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ
በገና ጨዋታ የለም ሎሌ ጌታ
የኔማ ጌታ የሰጠኝ ሙክት
ባለቦቃ ነው ባለምልክት
መስከረም ጠባ እሱን ሳነክት

ልጆች ደግሞ ‹‹ፍየሌን ነብር በላት፤ ለገና ብየ ሳደላድላት...›› እያሉ ይጫወታሉ። ‹‹ማታ ነው ድሌ ይሄ ነው አመሌ›› በማለት ሌሎች የፍቅር ዘፈኖችም ይዘፈናሉ።

ታህሳስ ገሠገሠ ከተፍ አለ ገና
እጠብቅሀለሁ አንተ ልጅ ቶሎ ና
ይወዘውዘኛል አልጠላኝም ገና
ፍቅር ሞገደኛው እየነሳኝ ጤና።
ምግብ አያስበላ አያስለብስ ልብስ
ሞገደኛው ፍቅሩ ይዞኝ በታህሳስ።
በማለዳ ጀንበር በገና ጨረቃ
እኔን እኔን ብላ መጣች ተደብቃ።

የገና ጨዋታ ወጥ የሆነ ህግ የለውም፤ ከአካባቢ አካባቢ እንዲሁም በከተማና በገጠር የተለያየ ህግ ሊኖረው ይችላል። የሚያስፈልገው የተጫዋች ቁጥር ሲሞላ ወገን ወገናቸውን ይዘው በዱላ ቀልጣፋ የሆኑ ተጫዋቾች ጥንጓን (መጫወቻ ኳሷ) ወደፊት እንድትቀጥል ይመቷታል ወይም ይመልሷታል። ተጫዋቾች ብዙ ጊዜ በጨዋታው ስለሚሰጡ ጥንጓን ከእግር መካከል በገባች ጊዜ ከሰው እግር ጋር ደርበው ስለሚመቱ የእግር መሰበር በዚህም ሳቢያ ወገን ለይተው እስከመፈናከት ይደርሳሉ። በንጉሳውያን ዘመን የመኳንንቱም አሽከሮች፣ የንጉሡና የንግሥቲቷ አሽከሮች የጌቶቻቸውን ስም በጉብዝና የሚያስጠሩት በባህላዊው የገና ጨዋታ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ጨዋታው በመጨረሻ ፀብ ስለሚያነሳ ጉዳት ያጋጥማል። ጥንጓም ኃይለኛ ለጊ በመታት ጊዜ ዐይን እስከ ማጥፋት ትደርሳለች። ተጫዋቾች ‹‹ሚና›› ብለው በሚጫወቱበት በቆልማማ ዱላ ቢደባደቡም የሚገላግል ዳኛ አልነበረም፤ ጨዋታውን በሚመለከቱ አባቶችም በድብድብ ከመሳቅ በስተቀር ሽምግልናቸው ለገና ጨዋታ አልተለመደም። ‹‹እግር ይብሳል፣ ያንከላውሳል›› እያሉ ማስፈራራት፣ ራስን መቀወር ወይም እንቆራቆስ ብሎ እጅና እግርን በዱላው መምታት በገና ጨዋታ የተለመደ ነበር።

በገና ጨዋታ አሸናፊ ለሆኑት ቡድኖች ፈሪዳና ጠጅ ተሰጥቷቸው እየበሉና እየጠጡ፣ እየዘፈኑ ሲሸልሉና ሲያቅራሩ ሜዳውን የጦርነት ድል ያገኙበት ያስመስሉት ነበር። ከሚዘፍኑትና ግጥሞች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ማታ ነው ድሌ
ይሄ ነው አመሌ
አሲና በል አሲና ገናዬ
ኦ! ጉ! አሲና በል አሲና ገናዬ
ግፋው ግፋው አለኝ እኔ እንደምን ልግፋው
የአንድ በሬ ጨጓራ እንደ ቅል የነፋው።
የብብቱ ሽታ
የመንፈቅ በሽታ።
የጀርባው መረሬ፣ ያውላል ጥንድ በሬ።
ከአሥር ጋን አተላ
አይተርፈው በአንኮላ።
እግርህ የሸረሪት ሆድህ የእንቁራሪት
ቀን እንደጠላሁህ እንዳትመጣ ሌሊት።

ስድብ ለተራው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመኳንንቱና በነገሥታቱም ላይ ሊሰነዘር ይችላል። በሚደርስባቸው ስድብ ግን ምንም ዓይነት ቁጣና ቅጣት አያደርጉም። ‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ፤ በገና ጨዋታ የለም ሎሌ ጌታ›› የተባለላቸውም ለዚህ ነው።

የገና በዓል መነሻውና የስነ ቃል ምንጩ ከገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ቢሆንም አሁን ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኗል። በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መንገድ የሚከበረው ከተማ ቦታ በተለይም አዲስ አበባ ነው። ለዚህም ምክንያቱ በገጠር አካባቢ ተገቢ የግንዛቤ ማስጨበጫ አለመሰጠቱ ነው። እንዲያውም በተቃራኒው ኋላቀርነት ነው እየተባሉ ስለሚነገሩ ለአገር ባህል እንዳይቆረቆሩና እንዳይጠብቁት ተደርጓል። ከተማ አካባቢ የሚኖረው ህዝብ በማንበብም ሆነ መገናኛ ብዙኃንን በመከታተል ባህል አኩሪ መሆኑን ግንዛቤ ስለሚኖረው ይመስላል ባህል ሁሉ ወደ ከተማ እየገባ ነው። በውጭው ዓለም እንኳን ለራሳቸው የሆነ ነገር ያላቸውን ክብር እናያለን። ዳሩ ግን የአገሪቱ አኩሪ ባህል ባለቤት የሆነውን የገጠሩ ማህበረሰብ ላይ አልተሰራም። ይህ ጉዳይ የሁላችንም ነውና ማወቅ ብቻ ሳይሆን ማሳወቅም ይጠበቅብናል!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ታዳጊዎች ፈተና

ሰሳማዊት ውቤ

ታዳጊ ከድር ቢላል ተወልዶ ያደገውና አሁንም ከሴት አያቱ ጋር የሚኖረው በሐረር ከተማ ነው።የኤች አይቪ ኤድስ ቫይረስ በደሙ ውስጥ መኖሩን ካወቀ አመታት ተቆጥረዋል። ቫይረሱ በደሙ ውስጥ መኖሩን የሰማው ልጆች ትምህርት በሹክሹክታ ሲያወሩ ነው ።በሁኔታው ሆድ ብሶት አያቱን መጥቶ ሲጠይቃቸው ቫይረሱ እንዳለበት አረዱት። እሳቸው ከሆስፒታል እያመጡለት በየቀኑ እንዲውጥ የሚያደርጉት መድሃኒትም የኤች አይቪ እንደሆነ ነገሩት።እሳቸው እያሳደጉት ያሉትም እናቱና አባቱ በበሽታው በመሞታቸው እንደሆነም አስረዱት።ነገሩ ግር አለው፤ መቀበል አልቻለም።



ታዳጊ ከድር ሁኔታውን ሲያስታውስ እንዲህ ይላል‹‹ከዚህ በኋላ ትምህርት ቤት ሄዶ መማር አስጠላኝ።ከወር በላይም ከትምህርት ቤት ቀረሁ።መድሃኒቱንም አልውጥም፤ ምግብ አልበላም ብዬ አያቴን አስቸገርኳት።ኤች አይቪ ገዳይ መሆኑን በትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያ ስለሰማሁ ልሞት ነው ብዬም ስለፈራሁ ሳላቋርጥ አለቅስ ነበር››ይላል።

አያቱ በግድ ወደ ሆስፒታል ወስደውት የምትከታተለው ሐኪም ከመከረችውና እንደማይሞት ከነገረችው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ ያቋረጠውን ትምህርት ቀጠለ።ታዳጊው እንደነገረን ግን ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ስለኤች አይቪ ሲወራ እሱን ይመስለው ስለነበር ይሸማቀቃል።በተለይ ከሰፈር ሰምተው ቫይረሱ በደሙ ውስጥ መኖሩን በሹክሹክታ ሲነጋገሩ የሰማቸው ልጆች ክፍሉ ውስጥ ስለነበሩ ዞር ብለው ሲያዩትና የሁሉም ተማሪ ዓይን ወደ እርሱ ሲወረወር ከክፍል በመውጣት እያለቀሰና እየሮጠ ወደ ቤቱ ሄዶም ያውቃል።

የህክምናውን ሁኔታ ለምትከታተለው ሃኪም ይሄን ከነገራት በኋላ አያቱን እንዲያመጣቸው አዘዘችው።ከዛም ሉብቻቸው ካወራቻቸው በኋላ ደብዳቤ ሰጠቻቸውና አብረውት ወደ ትምህርት ቤቱ ሄደው ለዳይሬክተሩ ሰጡት። ዳይሬክተሩ ክፍል ቀየረው።በቀጣይ ዓመት ሌላ ትምህርት ቤት እንደሚገባም ነገረው።በቀጣይ ዓመትም ሌላ በአቅራቢያው ያለ ትምህርት ቤት ገባ።ጎበዝ ተማሪ ሆኖም አንደኛ ለመውጣት መድሃኒቱን መውሰድ ቀጠለ፤አያቱ በእሱ ስም የሚያመጡትን መድሃኒት መውሰድ ቀጠለ፣ ተመጣጣኝ ምግብም በብዛት መመገብ ጀመረ።ቢሆንም እንደ ዱሮው ስለ ኤች አይቪ በትምህርት ቤት ውስጥ ሲወራ ባይሸማቀቅም ኤች አይቪ በደሙ ውስጥ መኖሩን ማንም እንዲያውቅበት አይፈልግም።

ታዳጊ ቤቢ ዳኔኤል በተመሳሳይ የሀረር ከተማ ነዋሪ ናት።ከህፃንነቷ ጀምሮ መድሃኒት እየዋጠች ነው ያደገችው።ታዳጊዋ እንደነገረችን ከፍ እያለች ስትመጣ የምትውጠው መድሃት የምን እንደሆነ እናቷን ስትጠይቃት የቲቪ መሆኑን ትነግራት ነበር።ቫይረሱ በደሟ ውስጥ መኖሩን ያወቀችው የምትውጠው መድሃኒትና የኤች አይቪ መድሃኒት ተመሳሳይ መሆኑን ትምህርት ቤት ውስጥ ቫይረሱ በደማቸው ያለ ተማሪዎች ከሚውጡት ጋር አስተያይታ ነው።

‹‹ለልጆቹ እኔም እንደዚህ ዓይነት መድሃኒት እውጣለሁ ስላቸው የኤች አይቪ እንደሆነ ነገሩኝ።ይሄን ለእናቴ ስነግራት ትክክል መሆኑን ነገረችኝ።››ቢሆንም እስከ 15 ዓመቷ ድረስ ቆይታ በዚህ አጋጣሚ ድንገተኛ መርዶ መስማቷ ደስተኛ አላደረጋትም።ምክንያቷን ስትናገር ‹‹ከልጆች ጋር ተደበድቤ በመሞንጨር ደምቼ አውቃለሁ።ስወድቅም ጉልበቴ ደምቶ የሚያውቅበት ጊዜ አለ።ከአፋችን ውስጥ ምግብ እያወጣን እንጎራረስ ነበር።ኤች አይቪ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው የሚተላለፈው ደግሞ በደምና በምራቅ አማካኝነት ነው።በተለይ ቫይረሱ በምራቅና በደም ውስጥ እንዳለም አውቃለሁ።በዚህ አጋጣሚ ለጓደኞቼ ቫይረሱን አስተላልፌ ሊሆን ይችላል›› ትላለች።

ቤቢ ስለዚህ ወላጆች ለልጆቻቸው ቫይረሱ በደማቸው እንዳለባቸውና የሚያውጧቸው መድሃኒትም የኤች አይቪ እንደሆነ ሊነግሯቸው ይገባል ባይ ነች።ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ግንዛቤ ካላቸው ከራሳቸው አልፈው ሌሎቹን ከቫይረሱ ይጠብቃሉ የሚል ምክር ታስተላልፋለች።

ሌላኛዋ ወጣት አክሱማዊት መዝሙር ትባላለች። 23 ዓመቷ ሲሆን የምትኖረው ሐረር ከተማ ውስጥ ከአባቷ ጋር ነው።ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ቢኖርም ከመማር ስላላገዳት በኪሊኒካል ነርሲንግ ተመርቃለች። ቫይረሱ በደሟ ውስጥ መኖሩን ያወቀችው የ14 ዓመት ታዳጊ ሆና ነው። ፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት መውሰድም ከጀመረች እንዲሁ 14 ዓመቷ ነው።

የዛሬ ሁለት ዓመት የተመሰረተው የህፃናትና ወጣቶች ማህበር መስራችና ሊቀመንበር ነበረች።ማህበሩ 98 ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ህፃናትን አቅፎ በመያዝ ነው የተመሰረተው።አባላቱ ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው በመሆናቸው ምክንያት በሕይወት ፋናና በጀብላ ህክምና ተቋም የምክር አገልግሎትና የሕክምና ድጋፍ የሚደረግላቸው ናቸው።ለአባላቱ የሐረር ጤና ቢሮ የደብተር፤የትራንስፖርትና ቡና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል።ግን መድሃኒቱ ምግብ ስለሚፈልግ የምግብ ድጋፍ የግድ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን አሁን የምግብ ድጋፍ ስለሌለ ህፃናትና ታዳጊዎች መድሃኒቱን መዋጥ ይከብዳቸዋል።በዚህም ምክንያት በሽታው የሚጠናባቸው ብዙ እንደሆኑ አክሱማዊት ትናገራለች።

ከዚህ ሁሉ የከፋው ግን ለህጻናቱ የሚወስዱት ምድሃኒት ምን እንደሆነ ብዙ ጊዜ አይነገራቸውም። የሚውጡት መድሃኒት አንድ ጊዜ የጉንፋን ሌላ ጊዜ ደግሞ የቲቪ ነው እያሉ በመዋሸት እንዲወስዱ የሚያደርጉ ልጆች ብዙ ናቸው። ይህ ደግሞ ቫይረሱ በደማቸው መኖሩ ዘግይቶ ሲነገራቸው ተስፋ በመቁረጥ ትምህርት አንማርም ምግብ አንበላም አልፎ ተርፎ ወላጆቻቸው ሁለቱም ወይም አንዱ ካሉ ለምን ወለዳችሁኝ የሚል ጥያቄ እንዲነሱ ምክንያት ይሆናል ።

ቫይረሱ በደማቸው መኖሩን ሌላ ሰው የሚያውቅባቸው የሚመስላቸውንና ራሳቸውን የሚያገሉም አሉ።መድሃኒቱን ቅዳሜ ቅዳሜ ሰው ሳያያቸው ልጆቹ ብቻቸውን ሆስፒታል ሄደው እንዲወስዱ ነው የሚደረገው።ሊደርስባቸው የሚችል አድሎና መገለልን በመፍራት ሚስጥራቸውም የተጠበቀ ቢሆንም እስከ መጨረሻው ግን ከሰው ደብቆ መኖር ግን አዳጋች ነው። ።በተለይ በየትምህርት ቤቶቹ ራሳችሁን ከኤች አይቪ ጠብቁ ተብሎ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉም ሰው የሚጠላቸው የሚመስላቸውና ራሳቸውን የሚያገሉ በርካታ ናቸው።አብዛኞቹ ልጆች ሁለቱንም ወላጆቻቸውን፤ አንዱን ወላጃቸውን በበሽታው ያጡና ከአንዱ ወላጃቸው ፤ከአያቶቻቸው ወይም ከዘመድ ጋር ተጠልለው የሚኖሩ ናቸው ብላናለች ወጣት አክሱማዊት።

# ዓለም አቀፍ

## ሳኡዲ አረቢያ ለእስያ ገዥዎች የድፍድፍ ነዳጅ ዋጋ ልትቀንስ ነው

ከፍተኛ የነዳጅ ላኪ ከሆኑ አገራት አንዷ የሆነችው ሳኡዲ አረቢያ ለእስያ ገዥዎች በ15 ወራት ውስጥ የድፍድፍ ነዳጅ የዋጋ ቅነሳ ልታደርግ እንደምትችል ተገለጸ። ሳዑዲ የዋጋ ቅነሳ የምታዳርገው የዓለም የነዳጅ ገበያ ላይ ባለው ከመጠን በላይ አቅርቦት ምክንያት ነው ተብሏል።

በተለይም ነዳጇን በአውሮፓ ምድር እንዳትሸጥ እገዳ የተጣለባት ሩሲያ የነዳጅ ምርቷን ወደ እስያ ገበያ መላክ መጀመሯ ሳዑዲ አረቢያ በነዳጅ ዋጋ ላይ ቅነሳ እንድታደርግ አስገዳጅ ሁኔታ እንደፈጠረባት ይነገራል። በዚህም መሰረት ግዙፉ የነዳጅ ኩባንያ ሳዑዲ አራምኮ በዱባይ ቤንችማርክ ከተወሰደው እርምጃ ጋር በተያያዘ በየካቲት ወር የመሸጫ ዋጋውን በበርሚል በ1 ነጥብ 50 ዶላር ሊቀንስ ይችላል እንደሚችል ተመላክቷል።

የዋጋ ማስተካከያው በህዳር 2021 መጨረሻ ወደ ነበረው ዋጋ የሚመልስና ከዱባይ የዋጋ ማነጻጸሪያ አኳያ የ1 ነጥብ 75 ዶላር ብልጫ እንዲኖረው የሚያደርግ ነው። ሳዑዲ አራምኮ የድፍድፍ ነዳጅ የዋጋ ተመን የሚያወጣው ከደንበኞች በሚሰጡ ምክሮች እና በዘይት ዋጋ ላይ ባለፈው ወር ላይ የተደረገውን ለውጥ በማስላት በምርቶች ዋጋ ላይ በመመስረት ነው።

ሮይተርስ ያነጋገራቸው አንድ አንድ ምላሽ ሰጪ “የቅርብ ጊዜ የገበያ ሁኔታ ደብዝዟል፤ ብዙ የሩሲያ የነዳጅ በርሜሎች ወደ እስያ ይጎርፋሉ ተብሎ ቢጠበቅም ፍላጎት እየጨመረ አይደለም” ብለዋል። ለቻይና እና ህንድ ቀዳሚ ድፍድፍ አቅራቢ መሆን የቻለችው ሩሲያ ፤ አሁን ላይ የእስያው ገበያ ለመቆጣጠር እየታተረች እንደሆነም እየተነገረ ነው።

ምንም እንኳን ሞስኮ ባለፈው ሳምንት በሩሲያ ድፍድፍ ነዳጅ ላይ የዋጋ ጣሪያን በመወሰን በተሳተፉ ሀገራት የድፍድፍ ነዳጅ ሽያጭ ብታግድም ፤ በእስያ የሚገኙ ቁልፍ የነዳጅ ደንበኞቿ የዋጋ ማሻሻያ ጥምረትን ባለመቀላቀላቸው ነዳጅን ካለምንም



ችግር በማቅረብ ላይ መሆኗን አል ዐይን ዘግቧል።

ከሩሲያ -ዩክሬን ጦርነት ጋር በተያያዘ ከምዕራበውያን ጋር የነበራት የንግድ ልውውጥ ሙሉ በሙሉ ያቋረጠችው ሞስኮ፤ የተጣሉባት ማዕቀቦች የማይነሱ ከሆነ ወደ አውሮፓ ነዳጅ እንደማትልክ መግለጿ አይዘነጋም።

## የታንዛኒያ መንግሥት ፖለቲካዊ ሰልፍ ማድረግ የሚያግደውን ሕግ አነሳ

የታንዛኒያው ፕሬዚዳንት ሳሚያ ሱሉሁ ሐሳን በአገሪቱ ለስድስት ዓመታት ተጥሎ የነበረውን ፖለቲካን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሰልፍ ማድረግ የሚከለክለውን ሕግ አንስተዋል።ከእርሳቸው ቀደም ብሎ የነበሩት ፕሬዚዳንት ጆን ማጉፉሊ ሥልጣን ከያዙ በኋላ እአአ 2016 ፖለቲካን የተመለከቱ ሰልፎችን አግደው ነበር። ምክንያታቸውም ሰልፎቹ በቀላሉ ወደ ሁከት ያመራሉ የሚል ነበር።

የቪኦኤው ቻርለስ ኮምቤ ከዳር ኤስ ሳላም እንደዘገበው ፕሬዚዳንቷ ሳሚያ የሕጉን መነሳት ያስታወቁት ከፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ጋር ባደረጉት ስብሰባ ላይ ነው።የቀድሞው ፕሬዚዳንት ጆን ማጉፉሊ ከአንድ አመት በፊት በሞት ሲለዩ ወደ ሥልጣን የመጡት ሳሚያ ሃሳን የፖለቲካ ተቀናቃኝን ያፍናል ከሚባለው የማጉፉሊ ፖሊሲ እንደሚለዩ ለማሳየት በርካታ እርምጃዎችን ወስደዋል።

አንዳንድ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች እንደሚሉት የፕሬዚዳንቷ እርምጃ በአገሪቱ ለሚገነባው ዲሞክራሲ



የመሠረት ድንጋይ ሊሆን ይገባል።ፕሬዚዳንት ሳሚያ ከዚህ በፊት ባደረጉት ንግግር በታንዛኒያ ዋና ዋና አንገብጋቢ ያሏቸውን ጉዳዮችን አንስተው ነበር። በተለይም ዲሞክራሲንና እየጨመረ የመጣውን ለለዉጥ ያለውን ተስፋ በተመለከተ።

እነዚህን ለውጦች በተግባር ለማዋል ፈተና ሊገጥማቸው እንደሚችል የቪኦኤው ቻርለስ ኮምቤ ዘገባ አመልክቷል። ፕሬዚዳንቱ የተለየ አቀራረብ ቢኖራቸውም፣ እርሳቸውም ሆኑ የቀድሞው ፕሬዚዳንት የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ዓባል ናቸው። በመሆኑም የፓርቲያቸው ድጋፍ ያሻቸዋል ሲል ቪኦኤ ዘግቧል።

# ስፖርት





## ጥሩነሽ ዲባባ ከአራት ዓመት በኋላ ወደ ውድድር ልትመለስ ነው



አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ከረጅም አመት በኋላ ወደ ውድድር ተመልሳ በሂውስተን ግማሽ ማራቶን ትሳተፋለች፤

የምንጊዜም ድንቅ የረጅም ርቀት አትሌት የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ከአራት አመታት በኋላ ወደ ውድድር ትመለሳለች። ሶስት የኦሊምፒክ ወርቅ ሜዳሊያዎችና የበርካታ የአለም ቻምፒዮናዎች አሸናፊዋ ጥሩነሽ ከረጅም ጊዜ በኋላ ወደ ውድድር ስትመለስ የመጀመሪያ ውድድሯን በሂውስተን ግማሽ ማራቶን ለማድረግ ከአስር ቀን በኋላ ቀጠሮ መያዟ ታውቋል።

እኤአ በ2018 የመጨረሻ ውድድሯን ያደረገችው ጥሩነሽ በወሊድና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ከውድድሮች ርቃ የቆየች ሲሆን ዘንድሮ ግን ወደ ጎዳና ላይ ውድድሮች ፊቷን መልሳ በአትሌቲክስ ህይወቷ ተጨማሪ ስኬት ለማስመዝገብ እንደምትሮጥ የሂውስተን ግማሽ ማራቶን አዘጋጆች ያወጡት መግለጫ ይጠቁማል።

“ ሂውስተን የምወደው ውድድር ነው፣ ዝግጅቴም በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው፣ ያለኝን አቅም ለመፈተሽና የቀጣይ የአትሌቲክስ ህይወቴን ምእራፍ ለመወሰን ይህ መልካም አጋጣሚ ነው” በማለትም የ2017 ቺካጎ ማራቶን አሸናፊዋ ጥሩነሽ አስተያየት ሰጥታለች።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ የጎዳና ላይ ውድድሮች እየታየች የምትገኘው የጥሩነሽ ዲባባ ታናሽ እህት እና ዲባባም በዘንድሮው ሂውስተን ግማሽ ማራቶን ከእህቷ ጋር እንደምትወዳደር ታውቋል። ከሁለቱ እህትማማቾች ጎን ለጎን በ2021 የበርሊን ማራቶን ሁለተኛ ሆና ያጠናቀቀችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ህይወት ገብረኪዳን ተወዳዳሪ እንደምትሆን ይጠበቃል። የ2022 የአለም ቻምፒዮና ላይ አራተኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀችው ኤርትራዊቷ አትሌት ናዝሬት ወልዱም የዘንድሮው ሂውስተን ግማሽ ማራቶን ፉክክር አካል ሆናለች።

ፈጣን ሰአት ይመዘገብበታል ተብሎ በሚጠበቀው የዘንድሮው የሂውስተን ግማሽ ማራቶን ውድድር በሁለቱም ጾታ አሸናፊ የሚሆኑ አትሌቶች ከአስር ሺ ዶላር ጀምሮ ሽልማት እንደሚያገኙ የውድድሩ አዘጋጅ ኮሚቴ አሳውቋል።

የ37 ዓመቷ ድንቅ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ የዓለማችን የምንግዜም ምርጥ የረጅም ርቀት ሴት ለመባል በመም ውድድሮች በርካታ ታሪኮችን መስራት የቻለች ሲሆን ወደ ጎዳና ላይ ውድድሮች በተለይም ወደ ማራቶን ፊቷን ካዞረች ወዲህም ስኬቷ ቢቀጥልም በተለያየ ምክንያት ከውድድር ርቃ ቆይታለች። ያምሆኖ በኦሊምፒክ፤ በዓለም ቻምፒዮና ፤ በዓለም አገር አቋራጭ ውድድሮች የሰበሰበቻቸው ሜዳልያዎችና አጠቃላይ ውጤቶቿ በረጅም ርቀት ታሪክ ከሚጠቀሱ የዓለም ምርጦች ተርታ ያሰልፉታል። ይህ ክብረወሰኗ ከዚህ በኋላ በማራቶን ምርጥ ውጤቶች እየታጀበ የሚቀጥል ከሆነም የምንግዜም ምርጥ የረጅም ርቀት ሴት አትሌት ለሚለው የክብር ማዕረግ የሚቀናቀናት ላይኖር ይችላል። ጥሩነሽ በኦሊምፒክ እና የዓለም ቻምፒዮና በተጎናፀፈቻቸው ሜዳልያዎች ቁጥር የኢትዮጵያ ከፍተኛውን ውጤት ያስመዘገበች ሴት አትሌት እንድትሆን አስችሏታል።

ጥሩነሽ እኤአ በ2017 በ37ኛው የለንደን ማራቶን በሩጫ ዘመኗ ሁለተኛውን የማራቶን ውድድር አድርጋ ሁለተኛ ደረጃን ይዛ ስታጠናቅቅ ያስመዘገበችው 2፡17፡56 አዲስ የኢትዮጵያ ማራቶን ክብረወሰን እንደነበር ይታወሳል። ይህም እኤአ በ2012 በለንደን ኦሊምፒክ ቲኪ ገላና ካሸነፈችበት 2፡18፡58 ሰዓት በ62 ሰከንዶች የተሻለ ነበር።

ጥሩነሽ ዲባባ በለንደን ማራቶን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈችው እኤአ በ2014 ሲሆን በወቅቱ 2:20:35 በሆነ ሰአት 3ኛ ደረጃን ይዛ ነበር ያጠናቀቀችው። ጥሩነሽ በ2017 የቺካጎ ማራቶን በወቅቱ የአለም ሶስተኛውን ፈጣን ሰአት አስመዝግባ ካሸነፈች በኋላ በ2018 የበርሊን ማራቶን ተሳትፋ ነበር። በዚህ ውድድር ፈጣን ሰአት ታስመዘግባለች ተብሎ ቢጠበቅም 2:18:55 ሰአት አስመዝግባ ሶስተኛ ሆና ነበር ያጠናቀቀችው። ያም ውድድር የመጨረሻ የማራቶን ውድድሯ ነበር።

## ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

የባለንብረቱ ስም ወሰኔለሽ ነጋሽ ተሽከርካሪ አይነት አውቶብስ የሰሌዳ ቁጥር- 3-03503 ደ/ህ ሞዴል KG-LH172V የሻንሲ ቁጥር LH172-0052251 የሞተር ቁጥር 5L-5028430 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ 3-03503 ደ/ህ ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በቁጥር አፖ/ወም/17/4520/15 በ04/04/2015 አመልክተዋል፡፡ ታርጋውን ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ አመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የጉራጌ ዞን ትራንስፖርት መንገድ ልማት መምሪያ**

## አማራ ክልል

ለአቶ ገረመው አሻግሬ

ባሉበት ከሳሽ ጀግናው መኮነን ተከሣሽ እነ ገረመው አሻግሬ መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ አቶ ገረመው አሻግሬ መከሰስዎን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልስዎን ለ25/05/2015 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የባህር ዳር አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

## ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ ሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር እና በተከሳሾች 1ኛ. ኢፋ አብዲ አበበ 2ኛ. ቻላቸው ይሳቅ 3. ሚካኤል ረጋሳ፣ 4. ኢትራኮም አይቲ ሶሉሽን 5. ታታ ኮንሰልታንሲ ሰርቪስ 6. ሱባሴግ የጥበቃ እና ጽዳት አገልግሎት ድርጅት መካከል ስላለው ክስ በተመለከተ ስሙ ታታ ኮንሰልታንሲ ሰርቪስ የተባለው ድርጅት መከሰሱን አውቆ መልሱን ይዞ በቀጠሮው ቀን 9/5/2015 በ4፡30 በችሎት ላይ እንዲቀርብ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ችሎት ቡድን**

የባለንብረቱ ስም ዳሪሙ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት የሠሌዳ ቁጥር 06112 ኮድ 4 ኦሮ የሊብሬ ቁጥር 0083481 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ባለንብረት ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በ11/03/2015 አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ታርጋውን ወድቆ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የኢሊባቡር ዞን መንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

በከሳሽ የኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እና በተከሳሾች 1ኛ እንዳለ ነዲ ቶላ 2ኛ አበራ ሰቦቃ የተባሉት ተከሳሾች በከባድ የውንብድና እና የሰው መግደል ሙከራ ወንጀል በኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 354142 ላይ ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡ በመሆኑም በ25/05/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ቀርበው እንዲከራከሩ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ እነሱ በሌሉበት ክርክር ተደርጎ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን አዟል፡፡

**በኦሮሚያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች- ወ/ሮ አበበች ዲሳሳ ሁንዴ እና ተጠሪ አቶ ዳዊት አብተው ሰይድ ያሉበትን አናውቅም ያሉ ስለሆነ በጋዜጣ ይጠሩልን ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም አቶ ዳዊት አብተው ሰይድ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም እራሳቸው ካለ ጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ አ/አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቦሌ ምድብ ችሎት**

በፍ/ባለመብት አስካለ አጥናፉ የፍ/ባለዕዳ እነ ብርሀኑ ገቢሳ

አቶ አየነው ልደቴ መካከል ስላለው የአፈፃፀም ክርክር ጉዳይ የፍ/ባለዕዳዎች መከሰሳችሁን አውቃችሁ በ19/05/2015 ዓ.ም. በሆነ ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ፌ/ከ/ፍ/ቤት 1ኛ ፍ/ብሔር ቀጥታ ክስ እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን ጉዳያችሁ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን አውቀው እንዲቀርቡ፡፡

**የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም እስክንድር ታዬ ወ/ሰማያት የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-45551 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNC57A477314 ሞዴል ZZ3257N3447A1 የሞተር ቁጥር 07101709882C የሊብሬ ቁጥር 007467/0293506 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 15/4/2015 አመልክተዋል።

ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

በአመልካች ወ/ሮ ራህመት ዘርጋ ሀሰን እና በተጠሪ አቶ ያህያ አዘዲን አሊ ኡስማን አልዳበር መካከል ባለው የባልና ሚስት የፍች ክርክር ጉዳይ ተጠሪ በ10/05/2015 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሔር ችሎት በ3፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሃና ጌታቸው ገ/መድህን መካከል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ ኢንቨስትመንት ምድብ 5ኛ ባ/ኢ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ በተከሳሽ/ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ እና ማስረጃቸውን በሬጅስትራል በኩል ለ04/05/2015 ዓ.ም በ4፡10 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በተጨማሪም ክስ ለመስማት 08/05/2015 ዓ.ም በ8፡20 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ጌት-አስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-07498 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር ZAHE3KAARR0052224 ሞዴል ZAHE3KAARR የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር E0095542 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 17/4/2015 አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ይፍረደው አብርሃም ተክሉ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-82059 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JT132LNH300013785 ሞዴል LN170L-CRMDXW የሞተር ቁጥር 2L-4850999 የሊብሬ ቁጥር 235526ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 17/4/2015 አመልክተዋል፡፡

ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የልደታ ቅ/ጽ/ቤት**